ሞጁል 12

የታክስ ስሌቶች እና ሌሎች ክፍያዎችን

ስለማስከፈል

ግንቦት 2014 ዓ-ም

ይዘት

ክፍል አንድ:- አጠቃላይ ሁኔታ

- ዋና ዓላማ
- ዝርዝር አላማ
- የሰነዱ ሽፋን
- የስልጠናው ወሰን
- የሥልጠና ተሳታፊዎች
- ስልጠናው የሚወስደው ጊዜ
- ትርጉሜ

ይዘት...

ክፍል ሁለት፡- የታክስ ስሌቶች

- በታክስ ከፋዩ ስለሚዘጋጅ የታክስ ስሌት
- በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት
- የስጋት የታክስ ስሌት
- የተሻሻሉ የታክስ ስሌት

ይዘት...

ክፍል ሶስት፡-ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመሰብሰብ፣ማስከፈል

- ታክስ ለመንግስት የሚከፈል ዕዳ ስለመሆኑ
- የታክስ መክፈያ ጊዜ ስለማራዘም
- የአከፋፈል ቅደም ተከተል
- ለታክስ አከፋፈል የሚቀርብ ዋስትና
- ለዘገየ ክፍያ የሚከፈል ወለድ
- የታክስ ስሌቶችን ስለማስፈጸም
- ሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት ጥያቄ
- ሀብትን ስለመያዝ
- በፋይናንስ ተቀማት የተቀመጠ ገንዘብና ንብረት ይዞ ስለማቆየት
- የንግድ ድርጅት ለጊዜው ስለማሸግ
- የማጭበርበር ወይም የታክስ ስወራ ሲፈጸም ስለሚኖር የታክስ ኃላፊነት እና
- ሌሎችም

1.1. ዓላማ

❑ ዋና ዓላማ

በታክስ አስተዳደር አዋጅ፣ደንብ እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ መመሪያዎች ዙሪያ ውይይት በማድረግ የታክስ ስሌት፣ሌሎች ክፍያዎች እና ተመላሽን ይገልጻሉ።

- የታክስ ስሌት ላይ የሚያጋጥሙ ስህተቶች የሚታረሙበትን መንገድ ይገልጻሉ፤
- ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበውን የራስ ታክስ ስሌት እንዲያሻሽል ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ይገልጻሉ፤
- ታክስን እና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል እና ለዘገየ ክፍያ የሚከፈል ወለድን ይገልጻሉ፤
- በሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት ይገልጻሉ፤
- ማካካሻ፣ ተመላሽ እና ከታክስ ዕዳ ነጻ ስለመሆን ይገልጻሉ።

1.2. ወሰን


- **የሰነዱ ሽፋን**

- የሰነዱ ሽፋን የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2009፣መመሪያ ቁጥር 144/2011፣142/2011፣138/2010፣6/2011 እንዲሁም 146/2011 ናቸው ።

- **የሥልጠና ተሳታፊዎች**

ሥልጠናው መሠረታዊ እንደመሆኑ ለግብር ከፋዩ እና በግብር ከፋዩ ድርጅት ለሚሠሩ በድርጅቱ ሠራተኝነታቸው የተረጋገጠላቸው ባለሙያዎች ይሰጣል።

- **ጊዜ**



- የታክስ ስሌት
- የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ማሻሻል
- በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት
- የስጋት የታክስ ስሌት
- የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ
- የታክስ ዕዳ
- ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት
- ሀብት
- ሀብት ማስከበር
- የቀን ገቢ

“የታክስ ስሌት”:- ማለት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ፣በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት፣የስጋት የታክስ ስሌት፣የተሻሻለ የታክስ ስሌት፣አስተዳደራዊ የታክስ ቅጣት ወይም ወለድ ስሌት ወይም በታክስ ሕግ መሠረት የሚደረግ ሌላ ማንኛውም ስሌት ነው።

2.1. በታክስ ከፋዩ ስለሚዘጋጅ የታክስ ስሌት/25/

- የራሱን የታክስ ስሌት የሚያዘጋጅ በታክስ ስሌት ማስታወቂያው የገለፀው መጠን ተፈጻሚ ለሚሆንበት የታክስ ጊዜ ዜሮን ጨምሮ ሊከፈል የሚገባውን የታክስ መጠን ስሌት እንዳቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል።

በታክስ ከፋዩ ስለሚዘጋጅ የታክስ ስሌት...

የራሱን የታክስ ስሌት የሚያዘጋጅ ታክስ ከፋይ በሠንጠረዥ “ለ” ወይም “ሐ” የሚገኝ ገቢ በዚሁ የታክስ ጊዜ ኪሣራ የገጠመው እንደሆነ በታክስ ስሌት ማስታወቂያው የገለፀው ኪሣራ ለማንኛውም የታክስ አስተዳደር አዋጅ ዓላማዎች ተፈጻሚ ለሚሆንበት የታክስ ጊዜ ያጋጠመውን ኪሣራ ስሌት እንዳቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል።

በታክስ ከፋዩ ስለሚዘጋጅ የታክስ ስሌት...

- ለአንድ የታክስ ጊዜ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ያቀረበ የራሱን የታክስ ስሌት የሚያዘጋጅ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ታክስ ከፋይ፣ በዚሁ የታክስ ጊዜ በግብዓት ላይ የከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ጠቅላላ መጠን የተጨማሪ እሴት ታክስ ከሚከፈልበት ሽያጭ ላይ ከሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ጠቅላላ መጠን የበለጠ እንደሆነ፣በታክስ ስሌት ማስታወቂያው የገለፀው የታክስ መጠን ለማንኛውም የታክስ አስተዳደር አዋጅ ዓላማዎች የታክስ ማስታወቂያው ተፈጻሚ ለሚሆንበት የታክስ ጊዜ ታክስ ከሚከፈልበት ሽያጭ ላይ ከሰበሰበው ታክስ በላይ የግብዓት ታክስ መክፈሉን የሚገልጽ የስሌት ማስታወቂያ እንዳቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል።

2.1.1 ታክስ ከፋዩ ራሱ ያዘጋጀውን የታክስ ስሌት እንዲሻሻል የሚጠይቅበት ሁኔታ /29/

“የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ማሻሻል”:- ማለት ታክስ ከፋዩ በራሱ ውሳኔ መጀመሪያ ባቀረበው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ላይ የተገለፀውን የታክስ መጠን በመጨመር ወይም በመቀነስ ወይም ሌ.ላ ለውጥ በማድረግ የሚያቀርበው ማሻሻያ ነው።

- የራሱን የታክስ ስሌት ያዘጋጀ ታክስ ከፋይ ያቀረበውን በራስ የተዘጋጀ የታክስ ማስታወቂያ ባለሥልጣኑ እንዲያሻሽልለት ለባለሥልጣኑ በማመልከቻ ሊያመለክት ይችላል።

ታክስ ከፋዩ ራሱ ያዘጋጀውን...

- ታክስ ከፋዩ ራሱ ያዘጋጀው የታክስ ስሌት እንዲሻሻልለት የሚያቀረበው ማመልከቻ፡-
  - ✓ ታክስ ከፋዩ ራሱ አዘጋጅቶ ባቀረበው የታክስ ማስታወቂያ ላይ ሊደረጉ ይገባል ብሎ የሚያምናቸውን ማሻሻያዎችና ማሻሻያዎቹን ማድርግ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያቶች በዝርዝር መግለጽ አለበት
  - ✓ ታክስ ከፋዩ ያቀረበው የታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን በፊት ባሉ አምስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በነበሩ የራስ የታክስ ስሌትቶች ላይ ለውጥ የሚያመጣ ከሆነ የሁሉም ዘመናት ታክስ ስሌት ማሻሻያ በአንድነት ሊያቀርብ ይችላል

ታክስ ከፋዩ ራሱ ያዘጋጀውን የታክስ ስሌት……

- የማመልከቻው ይዘት፡-

✓ የታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግ የተጠየቀበትን የታክስ ጊዜ እና ዓይነት

✓ ማሻሻያ የሚደረግበትን ጉዳይ እና ምክንያቱን

✓ ማሻሻያ እንዲደረግበት የተጠየቀው ጉዳይ የሚያስከትለው የገንዘብ ወይም ሌላ ለውጥ

✓ የሚሻሻለው የታክስ ስሌት የተገለጸው የታክስ መጠን ወይም ወደፊት የሚሸጋገር ኪሳራ ወይም በብልጫ የተከፈለ የግብይት መጠን የሚገልጽ መሆን አለበት

ታክስ ከፋዩ ራሱ ያዘጋጀውን የታክስ ስሌት……

- የራስ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ እንዲሻሻል የሚቀርበው ማመልከቻ ከማሻሻያ ምክንያቶቹ ጋር አስፈላጊ ከሆኑ ሰነዶች ጋር ተያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል።
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የራስ የታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግበት የሚያቀርብለትን ማመልከቻ ተቀብሎ ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ ባሉት 120 ቀናት ውስጥ መርምሮ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የቀረበለትን የራስ ታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ተቀብሎ ማሻሻያው እንዲደረግ ወይም ማመልከቻውን ውድቅ በማድረግ ሊወስን ይችላል

ታክስ ከፋዩ ራሱ ያዘጋጀውን የታክስ ስሌት……

- የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የውሳኔ አሰጣጥ፦
  - ✓ በቀረበለት ማመልከቻ መሠረት የራስ የታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግለት የፈቀደ እንደሆነ የታክስ ስሌቱን በማሻሻል ለታክስ ከፋዩ የተሻሻለውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ይልክለታል
  - ✓ የቀረበውን የራስ የታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ያልተቀበለትን ምክንያት በመግለጽ በጹሁፍ ለታክስ ከፋዩ ያሳውቃል

ታክስ ከፋዩ ራሱ ያዘጋጀውን የታክስ ስሌት እንዲሻሻልለት ሲያመለክት በሚከተሉት ምክንያቶች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሊያሻሽልለት ይችላል፦

- የድምር ስህተት ሲኖር፣ የአጻጻፍ ስህተት ሲያጋጥም
- የሂሳብ መደብ አመራረጥ (chart of account) ጋር የተያያዘ ስህተት ሲኖር
- የጆርናል ምዝገባ ስህተት ሲኖር፣ሂሳብ ወደ ሌጀር ሲተላለፍ የተከሰተ ስህተት ሲያጋጥም ፣የሀሳብ ማስተካከያ(**Adjusting Entry**) ጋር የተያያዘ ስህተት ሲያጋጥም
- በሂሳብ መዝገብ ላይ ሳይመዘገብ የተዘለለ የገቢና ወጪ ሰነድ ሲኖር

የታክስ ስሌት የሚሻሻልበት.....

- የመጀመሪያ ወይም የመጨረሻ የሀብት ቆጠራ አያያዝ ስህተት ሲኖር
- የሂሳብ አያያዝ ዘዴ ስህተት ሲያጋጥም
- በታክስ ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የወጪ ኦዲተሮችን የኦዲት ሪፖርት ሲመረምር ባገኘው ግኝት መሠረት የሚደረግ ማስተካከያ ሲያጋጥም
- ሶስተኛ ወገን በሚሰጠው ማረጋገጫ ወይም በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ መሠረት በሂሳብ መዝገቡ ላይ ማስተካከያ ማድረግ ሲያስፈልግ

የታክስ ስሌት የሚሻሻልበት.....

- በታክስ ህግ ያልተፈቀደ ወጪ በተቀናሽ በመያዙ ምክንያት የተፈጠረ ስህተት ሲኖር፣ የግልና የንግድ ሂሳቦች በመቀላቀላቸው የተፈጠረ ስህተት ሲያጋጥም
- በታክስ ማስታወቂያ ቅጽ ላይ የአመዘጋገብ ወይም የአገላለጽ ስህተት ሲያጋጥም
- በታክስ ወይም በተለይ በኤክሳይዝ ታክስ የሂሳብ አያያዝ ላይ የማምረቻ እና የአስተዳደራዊ ወጪዎች ተፋልሰውና ባልተገባ ቦታ ላይ ተመዝግበው ሲገኙ እና
- የሚከፈለው የታክስ መጠን ላይ ለውጥ ሊያስከትል የሚችል አሳማኝ ምክንያት ሲያጋጥም ስራ አስኪያጁ የራስ የታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግ ሊፈቅድ ይችላል።

- ሚኒስቴሩ የመጀመሪያ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ(official assessement notice) ከሰጠ በኋላ ወይም አዲት በመደረግ ሂደት ላይ የሚገኝ ከሆነ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የራስ የታክስ ስሌት ማሻሻያ (amendment of self assessement) ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም
- አንድ ጊዜ የታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲደረግ ጥያቄ የቀረበበት የራስ ታክስ ስሌት በድጋሚ ማሻሻያ እንዲደረግበት ጥያቄ ሊቀርብበት አይችልም

የታክስ ስሌት ማሻሻያ የሚከለከልባቸው.....

- በግብር ዘመኑ ከፍተኛ የስጋት ደረጃ የተመደበ የታክስ ከፋይ የሚያቀርበው የታክስ ስሌት ማሻሻያ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም ።
- ሚኒስቴሩ በራሱ አነሳሽነት የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ሊሰጠው ይችላል ።

2.1.3 የተሻሻለ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ በድጋሚ ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ ታክስ ከፋዩ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የራስ ታክስ ስሌት እንዲሻሻል ወስኖ የተሻሻለውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከሰጠ በኋላ፤ለታክስ ከፋዩ የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከመሰጠት አያግደውም።

ሙከራ አንድ

ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበውን የራስ ታክስ ስሌት እንዲያሻሽል ስለሚፈቀድበት ሁኔታ አስረዱ?

2.2. በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት /26/

“በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት”:- ማለት ማንኛውም የታክስ ከፋይ በታክስ ህግ መሠረት ማቅረብ የሚገባውን የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ እንደሆነ ወይም በግምት ከመወሰኑ በፊት ካላቀረበ ወይም የሂሳብ መዝገብ ሳያቀርብ ገቢውን ያስታወቀ ወይም ባለስልጣኑ በመለወጥ፣በመቀነስ ወይም በመጨመር የሂሳብ መዝገብ ያሻሻለ እንደሆነ በማንኛውም ጊዜ በሚያገኘው ማስረጃ መሠረት በማድረግ ታክስ ከፋዩ ሊከፍለው የሚገባውን የታክስ መጠን የሚገልጽ ስሌት ነው።

በግምት የሚከናወን ....

- ግብር ከፋዩ ምንም ዓይነት የሒሳብ መዝገብና ሰነድ ያልያዘ እንደሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሒሳብ መዝገቡን እና ሰነዱን ባለሥልጣኑ ያልተቀበለለው እንደሆነ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የግብሩን እና የታክሱን ልክ በግምት ይወስናል።
- በማንኛውም የታክስ ጊዜ መቅረብ የሚገባውን የታክስ ማስታወቂያ ያልቀረበ እንደሆነ ባለሥልጣኑ በማንኛውም ጊዜ የሚያገኘውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ ለታክስ ጊዜው ታክስ ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ በግምት ማስላት የሚችል ሲሆን

በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት.....

የግምት ስሌቱ የሚከተሉትን ይመለከታል:-

- በሠንጠረዥ “ለ” ወይም “ሐ” ኪሳራን በሚመለከት የታክስ ጊዜውን የኪሣራ መጠን፤
- በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሠረት በግብዓት ላይ በብልጫ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስን በሚመለከት ለታክስ ጊዜው በግብዓት ላይ በብልጫ የተከፈለውን የታክስ መጠን፤ እንዲሁም
- በሌላ ማንኛውም ሁኔታ ዜሮ መጠንን ጨምሮ በታክስ ጊዜው ሊከፈል የሚገባውን የታክስ መጠን።

በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት.....

- ባለሥልጣኑ፤ታክሱ በግምት ለተሰላው ታክስ ከፋይ የሚከተሉትን ዝርዝር ነጥቦች ያካተተ የታክስ ግምት ስሌት ማስታወቂያ መስጠት አለበት፦
  - ✓ እንደሁኔታው የተሰላውን የታክስ መጠን፣ወደፊት የሚሸጋገር የኪሣራ ወይም በብልጫ የተከፈለን የግብዓት ታክስ መጠን፤
  - ✓ በተሰላው ታክስ ላይ ሊከፈል የሚገባ የቅጣት መጠን ካለ፤
  - ✓ በተሰላው የታክስ መጠን ላይ ሊከፈል የሚገባ የዘገየ ክፍያ ወለድ መጠን ካለ፤
  - ✓ የታክስ ስሌቱ የሚመለከተውን የታክስ ጊዜ፤
  - ✓ ማስታወቂያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ30 (በሰላሳ) ቀናት ውስጥ ታክሱ፣ ቅጣቱ እና ወለዱ የሚከፈልበትን ቀን፤

በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት.....

- ✓ ቅሬታ ማቅረብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ጨምሮ በታክስ ግምት ስሌቱ ላይ ቅሬታውን የሚያቀርብበትን አኳኋን።

- ➢ የሚሰጠው የታክስ ግምት ስሌት ማስታወቂያ ታክሱን በሚቀጥለው የታክስ ሕግ መሠረት በተዘጋጀው የታክስ ግምት ስሌት ሊከፈል የሚገባው ታክስ የሚከፈልበትን ጊዜ ("የመጀመሪያው የታክስ መክፈያ ጊዜ" ተብሎ የሚጠቀስ) ሊለውጥ የማይችል ሲሆን፣የታክስ ክፍያው በመዘግየቱ ምክንያት የሚጣል ቅጣትና ወለድ መታሰብ የሚጀምሩት ከመጀመሪያው የመክፈያ ጊዜ አንስቶ ይሆናል።

በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት.....

- ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው በታክስ ስሌት ለሚሰበሰብ ታክስ ብቻ ሲሆን በባለሥልጣኑ የተዘጋጀ የታክስ ግምት ስሌት የደረሰው ማንኛውም ታክስ ከፋይ የግምት ስሌቱ የሚመለከተውን የታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታውን አያስቀርም።
- በባለሥልጣኑ የተዘጋጀ የታክስ ግምት ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከደረሰው በኋላ ለዚያ የታክስ ጊዜ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የታክስ ማስታወቂያ ለታክስ ጊዜው እንደቀረበ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ሆኖ አይቆጠርም።
- ባለስልጣኑ በማንኛውም ጊዜ በግምት ላይ የተመሠረተ የታክስ ሰሌት ሊያዘጋጅ ይችላል ።

2.2.1. የግምት ታክስ አሠራር መርህ /ሙ138/2010/

- በየወቅቱ የሚታየው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እና የዋጋ ግሽበት
- የታክስ ከፋይ በግብር ዓመቱ በአንድ ሠንጠረዥ ውስጥ ከሚወድቁ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ወይም የንግድ ዘርፎች ገቢ ያገኘ እንደሆነ ሁሉም ገቢዎች ተጣምረው የሚወሰኑ ሲሆን የሠንጠረዥ "ሐ" ገቢዎች ውስጥ ከንግድ ሥራ የተገኘ ገቢ እና የማዕድን ሥራ ገቢ የሚጣመሩ አይሆንም።
- በቀን ገቢ ግምት የሚሰላ ከንግድ ሥራ የተገኘ ገቢ የየዘርፉ በሥራ ቀናት መሠረት በማድረግ የግብር ዓመቱ የሽያጭ መጠን ይወሰናል።

የግምት ታክስ አሠራር መርህ...

- ጠቅላላ ገቢያቸው በባለሥልጣኑ ወይም ከሶስተኛ ወገን በሚገኝ መረጃ የሚወሰንባቸው ዘርፎች፣ በቀን ገቢ ግምት፣ በቁርጥ ግብር አወሳሰን ሥርዓት፣ ግብር የሚወሰን ሲሆን ከተዘረዘሩት ውስጥ ከአንድ በላይ በተመሳሳይ ወይም በተለያየ የንግድ ዘርፍ ሆኖ ገቢው በአንድ ሰንጠረዥ የሚወድቅ ገቢ ያገኘ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ገቢው በሚወድቅበት ሰንጠረዥ መጣኔ መሠረት ግብሩ ተሰልቶ ይወሰናል።

የግምት ታክስ አሠራር መርህ...

- በቀን ገቢ ግምት የሚሰላ ከንግድ ሥራ የተገኘ ገቢ ከዚህ ሞጁል ጋር አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከተውን የየዘርፉ በሥራ ቀናት መሠረት በማድረግ የግብር ዓመቱ የሽያጭ መጠን ይወሰናል።
- ዕቃዎች ወደ ሀገር በሚገቡበት ጊዜ፣ በሀገር ውስጥ ከሚፈጸሙ ክፍያዎች ላይ ተቀንሶ በቅድሚያ የተከፈለ ግብር እና በግብር ዓመቱ ተከፋፍሎ ለባለሥልጣኑ ገቢ የተደረገ ግብር በሚቀርበው ማስረጃ መሠረት ለግብር ዓመቱ ከሚከፈለው ግብር ላይ ይቀነሳል።

የግምት ታክስ አሠራር መርህ...

- ገቢው ከተመዘገበበት የግብር ዘመን ውጪ ዘግይቶ የተቀነሰና ለባለሥልጣኑ ገቢ የተደረገ የቅድመ ግብር ክፍያ በሚያስታውቅበት የግብር ዘመን የሚቀናነስ ሲሆን፣ እንዲቀናነስለት የሚያቀርብ ግብር ከፋይ የቅድመ ግብር ክፍያ ማስረጃ ከግብር ዘመኑ በፊት ለነበረው ገቢ የተቀነሰ መሆኑን በጽሑፍ መግለጽ ይኖርበታል።
- በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ተቀንሶ በቅድሚያ የተከፈለ ግብር መጠን የግብር ከፋዩን ሽያጭ መጠን ትክክለኛነት በማረጋገጥና በማነጻጸር በሽያጭ መጠን ላይ የሚያመጣው ለውጥ ካለ ለግብር አወሳሰን ጥቅም ላይ ይውላል።

2.2.2. የሠንጠረዥ “ሀ”፣ “ለ”፣“ሐ” እና “መ” ገቢን በግምት ስለመወሰን

❑ ከመቀጠር የሚገኝ መደበኛ ገቢን በግምት ስለመወሰን

- ከራሱ ገቢ ላይ ግብር የመቀነስ ግዴታ ያለበት ተቀጣሪን በሚመለከት:-
  - ✓ ከቀጣሪው በሚገኝ የተቀጣሪውን የገቢ መጠን መረጃ መሠረት በማድረግ።
  - ✓ ይህ መረጃ ከሌለ ተቀራራቢ ወይም ተመሳሳይ ቀጣሪ ድርጅቶች አማካይ የተቀጣሪ የገቢ መጠን በመውሰድ ይወሰናል።
  - ✓ ይህም ከሌለ ታክስ ከፋዩ ቀድሞ ሲያሳውቅ የነበረውን መረጃ በመውሰድ ይወሰናል።

ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን በግምት .....

- ከተቀጣሪ ገቢ ላይ ግብር የመቀነስ ግዴታ ያለበት ቀጣሪ ቀንሶ ገቢ ያላደረገውን ወይም ሳይቀንስ የቀረውን ግብር በግምት ለመወሰን ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሰጠውን መረጃ በመጠቀም የቅጥር ገቢ ግብር ይወሰናል።

- ለሁሉም የተሸከርካሪ ዓይነት ዝቅተኛ የሾፌርና የረዳት ደመወዝ በቁርጥ የሚወሰን ሲሆን የተሳቢ ተሸከርካሪ በመጫን አቅሙ የተመለከተው የሾፌርና የረዳት ደመወዝ ተወስዶ የመቀጠር ገቢ ይወሰናል። ይህ ቢኖርም የኮንስትራክሽን ተሸከርካሪ አከራይ ታክሱ በግምት የሚወሰን ሲሆን መደበኛ የግምት ግብር አወሳሰን ሥርዓት ለሾፌርና ለረዳት ደመወዝ ተፈጻሚ አይሆንም።

ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን በግምት.....

- ከመቀጠር የሚገኝ መደበኛ ያልሆነ ገቢን በግምት ስለመወሰን

በሀገሪቱ ፀንተው ባሉ ሕጎች ከታክሱ ነጻ የተደረጉ ገቢዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ሰው ከመቀጠር ከሚያገኘው ገቢ ላይ በዚህ መሠረት በግምት ይወሰናል፣

- ወሩ ውስጥ ሠራተኛው ያገኘውን የትርፍ ሰዓት ክፍያ በወሩ ከሚያገኘው ደመወዝ ላይ በመደመር ጠቅላላ በተገኘው ገቢ ላይ በሠንጠረዥ "ሀ" በተገለፀው መሠረት ግብር ይከፈልበታል።

ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን በማምት....

- የአገልግሎት ካሳ ክፍያ፣ የሥራ መፈለጊያ ክፍያ ወይም ማስጠንቀቂያ ባለመስጠት የሚሰጥ ክፍያ፣ ስንብቱ ሕጋዊ ባለመሆኑ የሚሰጥ ካሳ እና ክፍያዎችን በጊዜው ባለመፈጸም የሚከፈል ካሳ የክፍያው መጠን በስንብቱ ጊዜ ላገኘው የመጨረሻ መደበኛ ደመወዝ ተካፍሎ በተገኘው ቁጥር ልክ የተገኘው የወራት ብዛት ለእያንዳንዱ ወር ራሱን የቻለ የወር ደመወዝ ግብር አስልቶ በመደመር ግብር የሚሰላ ይሆናል።

ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን በግምት.....

- ✓ የወራት ብዛት = የክፍያ መጠን/የመጨረሻው ወር ደመወዝ
- ✓ ግብር = የአንድ ወር ግብር X የወራት ብዛት

- ➢ ሙሉ ወራትን ከሸፈነ በኋላ የሚገኘው የአገልግሎት ክፍያ ራሱን ችሎ እንደ አንድ ወር ደመወዝ የሥራ ግብር ይታሰባል።
- ➢ የዓመት ፈቃድ፣ ጉርሻ/ቦነስ/ እና የመሳሰሉት ክፍያዎች ተጠቃለው ከተደመሩ በኋላ ለ12 ተካፍለው የተገኘው ውጤት መደበኛ ደመወዝ ላይ ከተደመረ በኋላ የሥራ ግብሩ እንዲሰላ እና የተገኘው የሥራ ግብር ክፍያ ቀደም ሲል በወር ደመወዙ የከፈለው ግብር ተቀንሶ የእያንዳንዱ 12 ወር የግብር ልዩነት በመደመር ይሰላል።

ከመቀጠር የሚገኝ መደበኛ ገቢን በግምት.....

- ✓ ተጨማሪ የወር ገቢ = ክፍያዎች/12
- ✓ የወር ደመወዝ እና በተጨማሪ የወር ገቢ የተገኘውን ውጤት በመደመር ግብር ይሰላል።
- ✓ ከላይ በተገኘው ገቢ ላይ ግብር ከተሰላው በኋላ በመደበኛ ደመወዝ የተከፈለ ግብር ይቀነሳል።
- ✓ የእያንዳንዱ 12 ወር በተመለከተው አግባብ ተሰልቶ ይደመራል ወይም የደመወዙ መጠን አንድ ዓይነት ከሆነ የተገኘው ውጤት በ12 ተባዝቶ ይሰላል።

ከመቀጠር የሚገኝ መደበኛ ገቢን በግምት.....

ለምሳሌ፡-የXYZ ድርጅት በ2013 ዓ.ም ትርፋማ በመሆኑና ሠራተኞቹ ላሳዩት የስራ ተነሳሽነት የአንድ ወር ደሞወዛቸውን በቦነስ መልክ እንዲከፈላቸው ሰኔ 30/2013 ቢፈቅድ

የሠራተኛ ስም	በወሩ የተከፈለ	መስከረም	ህዳር	ሰኔ
አቶ አበበ	የወር ደመወዝ	9,500	9,500	9,500
	የትራንስፖርት/የመዘዋወሪያ አበል	3,000	3000	3000
	የትርፍ ሰዓት ክፍያ	500	800	1000
	ድምር	13,000	13,300	13,500

<u>በዚሁ መሠረት የግብሩ አሰላል፡-</u>

- የመስከረም ወር ግብር የሚከፈልበት ገቢ = ደመወዝ **9,500** + የመዘዋወሪያ አበል 800 + የትርፍ ሠዓት ክፍያ 500= **10,800**

ከመቀጠር የሚገኝ መደበኛ ገቢን በማምት.....

- የተከፈለ ግብር 10,800 **x 30% -955 =2,285**
- በቦነስ ክፍያ ወቅት የተገኘ ገቢ 10,800 +792**=11,592**
- መከፈል ያለበት ግብር 11,592x35%-1500 = 2557.2
- የመስከረም ወር የሚከፈል ግብር በልዩነት 2,285-2557.2= 272.2

➢ የህዳር ወር ግብር የሚከፈልበት **= 9500** +800 + 800 **=11,100**

- የተከፈለ ግብር 11,100 **x 35% -1500 =2,385**
- በቦነስ ክፍያ ወቅት የተገኘ ገቢ 11,100 +792**= 11,892**
- መከፈል ያለበት ግብር 11,892 x 35% -1500 =2,662.2
- የህዳር ወር የሚከፈል ግብር በልዩነት 2385 -2662·2 = 277.2

ከመቀጠር የሚገኝ መደበኛ ገቢን በማምት.....

- የሰኔ ወር ታክስ የሚከፈልበት ገቢ=**9,500**+800+1,000= 11,300
  - የተከፈለ ግብር 11,300 **x 35% -1500 = 2,455**
  - በቦነስ ክፍያ ወቅት የተገኘ ገቢ 11,300 +792=**12,092**
  - **መከፈል ያለበት ግብር 12,092 x 35%-1500 = 2,732.2**
  - **የሰኔ ወር የሚከፈል የሚከፈል ግብር በልዩነት2,732.2-2,455= 277.2**

ከመቀጠር የሚገኝ መደበኛ ገቢን በማምት.....

- ከነዚህ ወራቶች ውጪ የተከፈሉት ክፍያዎች ተመሳሳይ በመሆናቸው 9500+800 =10,300
  - 10,300 **x 30% -955 = 2,135**
  - 10,300+792 =**11,092 x 35% -1500 = 2,382.2**
  - **በአንድ ወር በልዩነት የሚፈለግ ግብር 2,382.2-2,135 = 247.2 ሲሆን ተመሳሳይ የሆኑትን በማባሳት ተመሳሳይ ያልሆኑትን በመደመር 247.2x9= 2,224.8+272.2+277.2 +277.2 = በ2013 በጀት ዓመት ለተከፈለው የቦነስ ክፍያ ጠቅላላ በልዩነት 3,051.2 ግብር ይከፈላል።**

የቤት ኪራይ ገቢ ግብርን በማምት ስለመወሰን ፡-

- በአከራይና በተከራይ መካከል የተፈጸመ የኪራይ ውልን መሠረት በማድረግ፣ታክስ ከፋዩ ያቀረበው ማስረጃ ተአማኒነት ከሌለው፣ ከ3ኛ ወገን መረጃ ጋር ተመሳክሮ የተሻለው ተወስዶ ግብር ሊወሰን ይችላል
- በኪራይ ውል እና ከ3ኛ ወገን በተገኘ መረጃ መወሰን ካልተቻለ በተመሳሳይ የሥራ ዘርፍና ደረጃ በባለሥልጣኑ አዲት የተደረገ ታክስ ከፋይ መረጃን ወቅታዊ የገበያ ዋጋን ለመወሰን ቤቶቹ ከሚገኙበት አካባቢ በአካል በመገኘት

የቤት ኪራይ ገቢ ግብርን በግምት.....

አካባቢያዊ የገበያ ሁኔታ በማጥናት ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ደረጃ ያላቸው እንደየከተማው ደረጃ ከሁለት እስከ ሦስት ቤቶች ወርሃዊ የኪራይ አማካይ ዋጋ በመውሰድ ግብሩን ለመወሰን መሠረት አድርጎ መጠቀም ይቻላል።

- ቤቱ የተከራየው ከመኖሪያ አገልግሎት ውጭ በሚሆንበት ጊዜ ለኪራይ ገቢ የግምት አወሳሰን ጥቅም ላይ የዋለው የገቢ መጠን እንደአግባብነቱ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም ለተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰን መሠረት ሊሆን ይችላል

የቤት ኪራይ ገቢ ግብርን በግምት.....

- የደረጃ “ሀ” እና “ለ” ግብር ከፋይ ግብሩ በግምት በሚሰላበት ጊዜ ከግብር ዓመቱ ጠቅላላ የኪራይ ገቢው 35% እንደ ወጪ ተይዞ 65% ግብር የሚከፈልበት ገቢ ሆኖ በሠንጠረዥ “ለ” መሠረት ይሰላል።
- የደረጃ “ሀ” እና “ለ” የቤት ኪራይ ገቢ ግብር ከፋይ የሆነ ግብሩ በግምት የሚሠራ ከሆነና ከአንድ ዓመት በላይ የሚሸፍን የኪራይ ክፍያ የተቀበለ እንደሆነ የኪራይ ገቢው በግብር ዘመኑ ተጠቃሎ ተይዞለት ግብሩ ገቢው ለሚሸፍናቸው ዓመታት ተሸንሽኖ በመጣኔ መሠረት እንዲከፍል ይደረጋል።

የቤት ኪራይ ገቢ ግብርን በግምት

ለምሳሌ፡- አንድ የደረጃ“ሀ” አከራይ ድርጅት በ2014 በጀት ዓመት ለሶስት ተከታታይ አመታት የሚቆይ ለመጋዘን አግልግሎት የሚውል የህንጻ ኪራይ በ600 ሺህ ብር ቢያከራዩ

<u>የግምት ታክስ አወሳሰን ስሌት ሲሰላ</u>

- o 600,000/3=200,000 x 65% = 130,000
- o 130,000 x 30% = 39,000 x 3 ዓመታት =117,000
- o የተጨማሪ ዕሴት ታክስ 600,000 x15% = 90,000

የቤት ኪራይ ገቢ ግብርን በማምት

- ከአንድ ዓመት በላይ የሚቆይ የኪራይ ውል የውል ዘመኑ ከማለቁ በፊት የተቋረጠ እንደሆነና ለተከራይ ቀሪ ክፍያ መመለሱ በማስረጃ ሲረጋገጥ በብልጫ የከፈለው ታክስ ተሰልቶ ሊመለስለት ወይም ለቀጣይ ግብር ዘመን ታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ፍላጎቱን ሲገልጽ በታሳቢነት እንዲያዝለት ይደረጋል።

- ለታክስ ውሣኔ መሠረት የሚሆነው የሽያጭ ገቢ መጠን በግምት የሚወሰነው፡-

✓ ስለ ታክስ ከፋዩ ወርሃዊ/ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ታክስ ከፋዩ ያቀረበውን የሽያጭ መረጃ ወይም ከሥስተኛ ወገን መሠረት በማድረግ፣

✓ ስለ ታክስ ከፋዩ ወርሃዊ/ዓመታዊ የግዢ መጠን ከታክስ ከፋዩ /ከሥስተኛ ወገን መረጃ የተገኘ እንደሆነ የተገኘውን የግዥ መረጃ ያልተጣራ የትርፍ መቶኛን ተጠቅሞ ወደ ሽያጭ በመቀየር፤ሲሆን

የሠንጠረዠ “ሐ” ገቢ በግምት .....

- ✓ ቀመሩ የሚከተለው ይሆናል።

$$\text{ሽያጭ} = 100 \left[\frac{\text{ግዥ X 100}}{\text{ያልተጣራ ትርፍ መጣኔ}} \right]$$

- ✓ ከሦስተኛ ወገን መረጃ ሊገኝ በማይችልበት ሁኔታ ለታክሱ ስሌት መሠረት የሚሆነው ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ ከሚፈልግበት የሒሳብ ወር ወይም ቀጥተኛ የሆነ ታክስ ከሚከፈልበት የሒሳብ ዓመት በፊት ታክስ ከፋዩ ለከፈለው ታክስ መሠረት በሆነው ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢ መጠን ይሆናል።

- የታክስ ከፋዩን ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ለመወሰን ካልተቻለ:-
  - ✓ በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ ከሚገኝ ከታክስ አወሳሰን እና ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ቁጥጥር ቡድኖች የተዋቀረ ቢያንስ ሶስት አባላት ያሉት የገቢ ጥናት ኮሚቴ ታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራውን በሚያካሂድበት አካባቢ በአካል በመገኘት አካባቢያዊ የገበያ ሁኔታ ያጠናል።

- ✓ ጥናቱ ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ የንግድ ዓይነትና ደረጃ ያላቸው እንደየከተማው ደረጃ ከሁለት እስከ ሦስት ንግድ ቤቶች ያስታወቁትን ወይም የተወሰነባቸው ዓመታዊ አማካይ ጠቅላላ ገቢ በመውሰድ ያዘጋጀው አማካኝ የቀን ገቢ መረጃ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ወይም ለወከለው ኃላፊ ቀርቦ ሲጸድቅ ለታክስ አወሳሰን የሚያገለግል ይሆናል።

- ታክስ ከፋዩ በባለሥልጣኑ በተደረገ ክትትል ለግብይት ደረሰኝ ባለመስጠት በሚያዝ ሪከርድ በአንድ የግብር ዓመት ሶስት ጊዜ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው እንደሆነ ከላይ በተገለጸው መንገድ ታክሱ ይወሰናል።

- የታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራን በአካል ተገኝቶ ስለገቢው በሚጠናበት ወቅት የሚከተሉት ጉዳዮች ታሳቢ መደረግ አለባቸው:-
  - ✓ የንግድ ሥራው ያለበት አካባቢ ለንግዱ ሥራ ያለው አመቺነት፣ እንዲሁም የንግድ እንቅስቃሴውን ማገናዘብ፣
  - ✓ የድርጅቱ ሠራተኞች ብዛት እና የሚከፈላቸውን የደመወዝ መጠን፣
  - ✓ የንግድ ሥራው የሚሠራበት ቤት የኪራይ መሆን አለመሆኑንና የኪራይ ከሆነ የኪራይ መጠን፣
  - ✓ የድርጅቱን የመብራት፣ የውኃ እና የስልክ ፍጆታ ወጪ፣
  - ✓ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች አስተዳደራዊ ወጪዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

የሠንጠረዠ “ሐ” ገቢ በግምት .....

- የተገኘው መረጃ በቅደም ተከተል ጥቅም ላይ የሚውሉ ሆኖ ለደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች ጥቅም ላይ የሚውል የተጣራ የየንግድ ዘርፍ ትርፍ መጣኔን ለአወሳሰን ጥቅም ላይ መዋል አለበት።

- የግምት አወሳሰን ጥቅም ላይ የዋለው የሽያጭ መጠን እንደአግባብነቱ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም ለተርን ኦቨር ታክስ የግምት አወሳሰንም መሠረት በመሆን ያገለግላል።

የሠንጠረዥ “ሐ” ገቢ በግምት .....

- የታክስ ከፋዩን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በአካል ተጠንቶ በተገኘ መረጃ መሠረት ታክሱ የተወሰነ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሲሰላ ታክስ የተከፈለበት ግዥ ማስረጃ ላይ የተገለፀው የግብዓት ታክስ ይቀናነሳል።
- ግብርን በግምት የመወሰን ስልቶች ለግለሰብም ሆነ የሕግ ሰውነት ላላቸው ታክስ ከፋዮች ተፈፃሚ ይሆናል።

የሠንጠረዥ “መ” ገቢ በግምት ስለሚወሰንበት ሁኔታ

ሀብትን አልፎ አልፎ በማከራየት የሚገኝ ገቢ በግምት ስለመወሰን

- በባለሥልጣኑ ኢንተለጀንስ ወይም በተባባሪ አካላት ወይም በጥቆማ ከሶስተኛ ወገን የሚገኝ መረጃን በመጠቀም ሊወሰን ይችላል።
- አልፎ አልፎ ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ሀብት የሚያከራይ ግብር ከፋይ የገቢ መጠን መሠረት በማድረግ ሊወሰን ይችላል።
- ሀብቱ የሚገኝበት አካባቢ እና የታክስ መረጃ ሥርዓት መሠረት የሚገኝ መረጃ በመጠቀም ሊወሰን ይችላል።

2.2.3 መደበኛ የግምት አወሳሰን

የወፍጮ ቤት አገልግሎት ንግድ

- ከአንድ በላይ ቋት ያለው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ለማስላት ለቋቱ የተመለከተውን ግብር የሚከፈልበትን ገቢ መጠን በቋት መሠረት ተደርጎ ግብሩ የሚወሰን ይሆናል።
- የየቋቱ የምርት ዘመን የተለያየ በሚሆንበት ጊዜ የምርት ዘመናቸው በተመሳሳይ ምድብ ውስጥ የሚወድቅ ቋቶችን ሽያጭ መደመር እና በተለያየ የምርት ዕድሜ ምድብ የሚገኙትን ቋቶች ግብር የሚከፈልበትን ገቢ በማጣመር ግብሩን መወሰን ይገባል።
- የየቋቱ ተሰልቶ የተገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሠንጠረዥ “ሐ” የግብር መጣኔ መሠረት ግብሩ ተሰልቶ ይወሰናል።

መደበኛ የግምት አወሳሰን.....

የተሸከርካሪ ትራንስፖርት አገልግሎት ንግድ

- የትራንስፖርት ንግድ ሥራ ግብር የሚወሰነው ተሸከርካሪው የተመረተበት ዘመን መሠረት ተደርጎ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ:-
  - ✓ የህዝብ ማመላለሻ የሆኑ ትራንስፖርት ዓይነቶች በመቀመጫ ወንበር ብዛት፣
  - ✓ የደረቅ ጭነት ትራንስፖርት ዓይነቶች በጭነታቸው መጠን (በኩንታል)፣
  - ✓ የፈሳሽ ጭነት ትራንስፖርት ዓይነቶች በሚይዙት የፈሳሽ መጠን (በሊትር)፣
  - ✓ የተሳቢ ተሸከርካሪ የመጫን አቅም የሚወሰነው የጎታችና የተጎታች የመጫን አቅም ተደምሮ እንደ አንድ ተሸከርካሪ ተቆጥሮ፣
  - ✓ የጎታች ተሸከርካሪ የመጫን አቅም ለብቻው ሲሆን የመጫን አቅሙ በሊብሬው ላይ በተገለጸው መሠረት የሚወሰን ይሆናል ።

- ዓይነታቸውና የምርት ዘመናቸው የተለያዩ ተሽከርካሪዎች ያሉት ታክስ ከፋይ በየተሽከርካሪው የተገኝ ገቢ ተደምሮ የሚገኘው ጠቅላላ ገቢ በማትረፊያ ህዳጉ እየተሰላ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ጋር የሚደረስበት ይሆናል።
- ከአንድ በላይ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ያለው ግብር ከፋይ ግብር የሚከፍልበት ገቢ ተደምሮ በሠንጠረዥ “ሐ” መሠረት ግብሩ የሚሰላ ይሆናል።

- የተሸከርካሪው የግብር ዓመቱ ከፊል ጊዜ ብቻ ሥራ ላይ መዋሉ ከተረጋገጠ ከዓመት ገቢው ላይ በወራቱ ተሰልቶ ግብር እንዲከፍል ይደረጋል።
- የተሸከርካሪ ባለንብረት ራሱ የሚያሸከረክር ከሆነ ለሾፌር ይከፈል የነበረውን የደመወዝ ዓመታዊ ግብር ከተሸከርካሪ ዓመታዊ ግብር ጋር ተደምሮ ግብሩ ይከፍላል።
- የተሸከርካሪ ዓመታዊ ግብር በሚከፈልበት ጊዜ የረዳትና የሾፌር ከመቀጠር የሚገኘው ገቢ በአንድነት የሚከፈል ይሆናል።

የእርሻ አገልግሎት ተሸከርካሪ ንግድ

- ለእርሻ አገልግሎት የሚውል ተሸከርካሪ ንግድ ሥራ ግብር የሚወሰነው ተሸከርካሪው የተመረተበት ዘመን መሠረት በማድረግ ይሆናል።
- የእያንዳንዱ ተሸከርካሪ ዓይነት ዓመታዊ ገቢ፣ ግብር የሚከፈልበት ገቢና የግብር መጠን ስሌት በቁርጥ ግብር ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል፣

የኮንስትራክሽን መሣሪያ ኪራይ

- ታክሳቸው በግምት የሚወሰነው የኮንስትራክሽን መሣሪያ ባለቤትነት (ሊብሬ) በኮንስትራክሽን ሚኒስቴር አማካይነት የተሰጠውና ለኮንስትራክሽን ሥራ የሚከራይ ተብሎ የተገለጸ መሣሪያ ነው።
- የኮንስትራክሽን ተሽከርካሪ አከራይ ታክሱ በግምት የሚወሰነው ለትራንስፖርት ተሽከርካሪ እንዲያገለግል እንደየተሽከርካሪው የመጫን አቅም የተመለከተውን በመደበኛ የግምት ግብር አወሳሰን ሥርዓትን መሠረት በማድረግ ይሆናል።
- የኮንስትራክሽን መሣሪያ አከራይ ዝቅተኛ ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ መሠረት በማድረግ ግብሩ በግምት በሚወሰን ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ ይደረጋል።

ተ.ቁ	የማሽነሪው ዓይነት	የማሽነሪው ዓመታዊ የሽያጭ ገቢ በዕድሜ በብር	
		ከተፈበረከ እስከ 10 ዓመት	ከተፈበረከ ከ10 ዓመት በላይ የሆነው
1.	ኤክስካቬተር	422,400	211,200
2.	ሎደር	373,120	186,560
3.	ግሬደር	485,760	242,880
4.	ሮለር	253,400	126,720
5.	ዶዘር	563,200	281,600
6.	ሩሎ	399,872	199,936

- ከአንድ በላይ የኮንስትራክሽን ተሽከርካሪዎች ወይም የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች አከራይ የሆነ ግብር ከፋይ ለየመሣሪያው የተመለከተውን ዓመታዊ ገቢ መጠን ተወስዶ እንደአግባብነቱ ያለውን የማትረፊያ ህዳግ (የትርፍ መተመኛ መቶኛ) መሠረት በማድረግ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ተሰልቶ በሠንጠረዥ "ሐ" የግብር መጣኔ መሠረት ግብር ይወሰናል።
- የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ወይም ተሽከርካሪ ከ3ኛ ወገን ማስረጃ ማግኘት ከተቻለ መረጃው ተወስዶ ግብሩ ይወሰናል።

መደበኛ የግምት አወሳሰን.....

- የኮንስትራክሽን ተሽከርካሪ ወይም ማሽነሪ የሚያከራይ ታክስ ከፋይ እንደአግባብነቱ የተርን ኦቨር ታክስ ወይም የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል የሚጠበቅበት በመሆኑ ለማሽነሪው ወይም ለተሽከርካሪው የተቀመጠ ዓመታዊ የሽያጭ ገቢ መሠረት በማድረግ እንደአግባብነቱ የተርን ኦቨር ታክስ ወይም የተጨማሪ እሴት ታክስ ይወሰናል።

የልኳንዳ ንግድ

- በልኳንዳ ንግድ የተሠማራ ታክስ ከፋይ በግብር ዘመኑ፣ የዕርድ አገልግሎት የተሰጣቸውን የዕርድ ከብት ዓይነትና ብዛት የዕርድ አገልግሎት ከሚሰጥ ሰው በሚያቀርበው መረጃ መሠረት የሚሰላ ይሆናል።

- የሸማቾች የህብረት ሥራ ማህበራት፣ የቀበሌ መዝናኛ፣ የሠራተኛ ክበብ ውስጥ የሚገኝና በአነስተኛ ደረጃ የሚመደብ ልኳንዳ ቤት ከነማባያ ወይም ያለማባያ ለተጠቃሚ የሚያቀርበው አነስተኛ የሆነ ከብት ለመብልነት የሚውለው የሥጋ መጠን ለበሬ 84 ኪሎ ግራም፣ ለፍየል 10 ኪሎ ግራም እና ለበግ 8 ኪሎ ግራም እንደሆነ ተቆጥሮ እንደየከብቱ ዓይነት በባለሥልጣኑ በወቅታዊ አማካኝ የአንድ ኪሎ ሥራ የገበያ ዋጋ ተሰብስቦ በሚወሰነው መሠረት የሚሰላ ይሆናል።

- በመካከለኛ ደረጃ የሚመደቡ ልኳንዳ ቤቶች ከነማባያ ወይም ያለማባያ ለተጠቃሚዎች የሚያቀርቡት የከፍተኛ፣ መካከለኛ እና አነስተኛ የሆነ ከብት ለመብልነት የሚውለው የሥጋ መጠን አማካይ ለበሬ 122 ኪሎ ግራም፣ ለፍየል 16 ኪሎ ግራም እና ለበግ 9 ኪሎ ግራም እንደሆነ ተቆጥሮ እንደየከብቱ ዓይነት በባለሥልጣኑ በወቅታዊ አማካኝ የአንድ ኪሎ ሥጋ የገበያ ዋጋ ተሰብስቦ በሚወሰነው መሠረት የሚሰላ ይሆናል።
- የግመል ሥጋን በልኳንዳ ደረጃ የሚነግድ ታክስ ከፋይ በከፍተኛ ደረጃ የሚገኝ በሬ ለመብልነት የሚውለውን የሥጋ መጠን 173 ኪሎ ግራምን በመውሰድ በባለሥልጣኑ እየተሰበሰበ በሚወጣው በወቅታዊ አማካኝ የአንድ ኪሎ የግመል ሥጋ የገበያ ዋጋ የሚሰላ ይሆናል።

መደበኛ የግምት አወሳሰን.....

የውጭ ሀገር አሠሪና ሠራተኛ አገናኝነት ሥራ

- የውጭ ሀገር አሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ሥራ የሚሠሩ ሰዎች በሶስተኛ ወገን መረጃ መሠረት ተደርጎ ግብር የሚወሰንላቸው በሚከተለው መንገድ ይሆናል።
- ስለዘርፉ የሥራ እንቅስቃሴ ለግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ጥቅም ላይ የሚውሉ መረጃዎችን ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ፣ከአየር መንገድ፣ ከኢንሹራንስ፣ ከብሔራዊ ባንክ፣ከውጭ ጉዳይና ከሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት መረጃውን በማሰባሰብ ለዘርፉ በተቀመጠው የትርፍ መተመኛ መቶኛ መሠረት ግብር እንዲወሰን ይደረጋል።

መደበኛ የግምት አወሳሰን.....

- ከአሠሪ ሀገራት ተከፋይ የሚሆነውን የገንዘብ መጠን መረጃ በየግብር ዘመኑ ተለይቶ ለግብር አወሳሰኑ ጥቅም ላይ የሚውልበት ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኢትዮጵያ የውጭ ስምሪት አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲዎች በየሀገሩ የላኳቸውን ሠራተኞች ብዛት በየግብር ዘመኑ በመለየት በእያንዳንዱ ተጓዥ ዝቅተኛ የአገልግሎት ክፍያ እንደየሀገሩ ከሚመለከተው አካል በሚገኝ መረጃ በመውሰድ ይሰላል።
- በመረጃ ላይ የተመሠረተ የግቢ መጠን ለተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም ለተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰን መሠረት ይሆናል።

የንግድ ዘርፍ የማትረፊያ መጣኔ

- በመንግሥት የመግዣና መሸጫ ዋጋ በተተመነ የንግድ ዘርፍ (ስኳር፣ ፓልም ዘይት፣ ዱቄት፣ ጨው፣ ዳቦ እና ወዘተ) የተሠማራ ታክስ ከፋይ በመንግሥት በተወሰነለት አካባቢ እና ዋጋ ስለመሸጡ የሚገልጽ ደረሰኝ እና የምደባ መረጃ ያቀረበ እንደሆነ በሚመለከተው የመንግሥት አካል የተወሰነበት የትርፍ ህዳግ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ተደርጎ በመውሰድ ግብሩ ይሰላል።

- የዳቦ ቤት የሽያጭ መጠን ለማስላት በንግድ ሚኒስቴር በተደረገው ጥናት መሠረት፣ ኩንታል ዱቄት 1,000 /አንድ ሺህ/ ባለ 100 ግራም ዳቦ (አማካይ የዳቦ መጠን) ተወስዶ ለዳቦ ቤቱ ከመንግሥት አካል የተሰጠው የኩንታል ብዛት መረጃ በመውሰድ ባለሥልጣን የአንድ አማካይ ዳቦ (ባለ 100 ግራም) ወቅታዊና አማካይ የገበያ ዋጋን በመጠቀም ይወሰናል።

- በኮሚሽን ንግድ የተሠማራ ታክስ ከፋይ ጠቅላላ ገቢ ተደርጎ የሚወሰደው በኮሚሽን ስምምነት መሠረት በየምርት ወይም በአገልግሎት የሽያጭ ዋጋ ላይ የተጨመረ ወይም ከጠቅላላ ምርት ወይም የአገልግሎት ሽያጭ በመቶኛ የተወሰነው መጠን ይሆናል።

የንግድ ዘርፍ የማትረፊያ መጣኔ...

- በአከፋፋይነት/በጅምላ ንግድ የተሠማራ ታክስ ከፋይ:-
  - ከአምራች ጋር የተገባ የትርፍ ህዳግን የሚገድብ የጽሑፍ ስምምነት ሲኖር በስምምነቱ መሠረት ታክሱ ሊወሰን ይችላል።
  - ስምምነት በማይኖርበት ጊዜ ታክስ ከፋዩ በሚገኝበት አካባቢ የሚገኙ/በባለሥልጣኑ ዘንድ መረጃቸው የሚገኝ ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ በሆነ ሥራ የተሠማሩ ከ2 እስከ 3 ታክስ ከፋዮች ያስታወቁት/የተወሰነባቸውን መረጃ በመጠቀም ሊወሰን ይችላል።
  - ከላይ የተገለጸው መረጃ በማይኖርበት ጊዜ የታክስ ከፋዩ ጠቅላላ ገቢ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ የተወሰደ ግብር የሚከፈልበት ገቢን በማግኘት ሊወሰን ይችላል።

የንግድ ዘርፍ የማትረፊያ መጣኔ...

- ታክስ ከፋዩ ምርቱን ሙሉ በሙሉ ለቸርቻሪዎች ብቻ የሚሸጥ መሆኑን የሚገልጽ መረጃ ሲገኝ ለደረጃ “ሐ” ታክስ ከፋዮች የተቀመጠው የትይዩ ዘርፍ የትርፍ ህዳግ (50%) ተወስዶ የሚሠራ ይሆናል።
- ታክስ ከፋዩ ምርቱን ለቸርቻሪዎች እና ለሸማች የሚሸጥ መሆኑ የሚገልጽ መረጃ ሲገኝ ለደረጃ “ሐ” ታክስ ከፋዮች የተቀመጠው የትይዩ ዘርፍ የትርፍ ህዳግ 75% ተወስዶ የሚሠራ ይሆናል።
- ከመንግሥት ባለበጀት ተቋም ጋር የትርፍ ህዳግ ተወስኖ በሚከናወን ዕቃ ግዥ ወይም የአገልግሎት የአቅራቢው ግብር የሚከፈልበት ገቢ የሚወሰነው በግዥ ውል የተገለጸውን የትርፍ ህዳግን በመውሰድ ይሆናል።

የንግድ ዘርፍ የማትረፊያ መጣኔ...

- ከተገለጸው ውጭ የሚደረግ ግብይት የአቅራቢውን ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን በመደበኛ የትርፍ ህዳግ የሚሰላ ይሆናል።
- ሙሉ በሙሉ ምርቱን ለችርቻሪዎች እና ለሸማች በመሸጥ ገቢ ያገኘ ታክስ ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ተጣምሮ ታክሱ ይሰላበታል።

2.2.4. የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝን ታክስ በማምት የሚወሰንበት ሁኔታ

- ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 500 ሺህ በታች የሆነ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከ3ኛ ወገን በሚገኝ መረጃ ወይም አማካይ ቀን ገቢ ተገምቶ የሚወሰን ይሆናል።
- የደረጃ “ሐ” ታክስ ከፋይ በትይዩ የሚገኝ የንግድ ዘርፍ ማትረፊያ መጣኔ ተወስዶ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ይወሰናል።

የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝን ታክስ በግምት.....

- የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ:-
  - ✓ የትርፍ ህዳጉ በመንግሥት በሚወሰን የንግድ ዘርፍ የተሠማራ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ከሆነ የትርፍ ህዳጉ በሚመለከተው የመንግሥት ተቋም የተወሰነው የትርፍ ህዳግ ተወስዶ ወይም፣
  - ✓ ለባለበጀት የመንግሥት ተቋም የትርፍ ህዳጉ የተገደበ የጽሑፍ ስምምነት መሠረት በማድረግ ዕቃ ወይም አገልግሎት የሚቀርብ ሲሆን በስምምነቱ የተወሰነው የትርፍ ህዳግ ተወስዶ ግብር የሚከፈልበት ገቢ የሚወሰን ሲሆን ከነዚህ ውጭ የሚደረግ ግብይት የአቅራቢን ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን በመደበኛ የትርፍ ህዳግ የሚሰላ ይሆናል።

የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝን ታክስ በግምት.....

- ከላይ ከተገለጸው ውጭ የሚደረግ ግብይትን የአቅራቢን ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን በመደበኛ የትርፍ ህዳግ ይሰላል።
- ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢ ከብር 500 ሺህ/አንድ ሚሊዮን በላይ ሆኖ ገቢውን በሒሳብ መዝገብ ያላስታወቀ/ የሒሳብ መዝገብ ያላቀረበ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የግምት አወሳሰን ሥርዓቱ በቀን ገቢ ወይም በመረጃ ይወሰናል ።

2.2.5 በግምት የተወሰነ የታክስ ስሌት ስህተትን ስለማረም /85/

ባለሥልጣኑ በታክስ ሕግ መሠረት ለታክስ ከፋዩ የሰጠው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ በታክስ ሕግ ወይም በጉዳዩ ኩነቶች ላይ ትርጉም ጥያቄ የማያስነሳ የጽሑፍ፣የሂሳብ ስሌት ወይም ሌላ ማንኛውንም ስህተት የያዘ በሚሆንበት ጊዜ ባለሥልጣኑ ስህተቱን ለማረም ሲባል የታክስ ስሌት ማስታወቂያውን ወይም ሌላውን ሰነድ የታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ሰነዱ ለታክስ ከፋዩ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5/አምስት/ ዓመታት ውስጥ ማሻሻል ይቻላል።

በግምት የተወሰነ የታክስ ስሌት ስህተትን.....

- የታክስ ስህተት የሚባለው:-
  - ✓ የመደመር፣ የመቀነስ፣ የማባዛትና የማካፈል ስህተት፣
  - ✓ በስሌት ማጠቃለያ ላይ ከመንደርደሪያ ሀሳብ መለየት ወይም መቃረን፣
  - ✓ ከአንድ የሒሳብ ቁጥር ከፊት ወይም ከኋላ የቁጥር መጨመር ወይም መቀነስ ወይም የሒሳብ ቁጥር ቦታ መቀያየር (transposition)፣
  - ✓ የገቢ ወይም የወጪ ኮድ አመዘጋገብ ስህተት፣
  - ✓ የቃል ወይም የሐረግ በአዎንታ ወይም አሉታ መቀያየር፣
  - ✓ የሒሳብ ቁጥር ወይም ሀሳብ መተው ወይም መዘለል (omission)
  - ✓ ከግብር ነጻ የሆነ ገቢን ግብር በሚከፈል ገቢ ውስጥ መጨመር፣
  - ✓ የታክስ መጣኔን ወይም የትርፍ ህዳግን መሳሳት፣

በግምት የተወሰነ የታክስ ስሌት ስህተትን.....

- ✓ በአንድ ታክስ ከፋይ ሒሳብ ውስጥ የሌላ ታክስ ከፋይ ሒሳብ መጨመር ወይም ማቀያየር፣
- ✓ በታክስ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል፣ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በመደበኛ ፍ/ቤት እንዲስተካከል የተወሰነን ጉዳይ አለማስተካከል፣
- ✓ ስህተት ሊታረም የሚለው በታክስ ውሳኔ መጠን ላይ በመጨመር ወይም በመቀነስ ለውጥ የሚያመጣ ሲሆን ብቻ ሆኖ ለውጥ የማያመጣ በመሆኑ የማይታረም ስህተት ሲኖር ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ይገለጻል።

በግምት የተወሰነ የታክስ ስሌት ስህተትን.....

- በግምት የተወሰነ የታክስ ስሌት ቀጥሎ በተመለከተው መንገድ የሚታረም ይሆናል።

- ✓ የግምት ታክስ ስሌቱን የሠራው ሥራ ሂደት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከተሰጠ በኋላ በታክስ ስሌትና አወሳሰን ሂደት የተፈጸመ ግልጽና የማያከራክር ስህተት የፈፀመውን ባለሙያ ወይም የሌላ ባለሙያ አስተያየት ጭምር በማያያዝ ስህተቱ እንዲታረም የውሳኔ ሀሳብ ለቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ያቀርባል።

በግምት የተወሰነ የታክስ ስሌት ስህተትን.....

- ✓ የቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ስህተቱ እንዲታረም ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በአግባቡ መመርመር ያለበት ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የውሳኔ ሀሳብ ያቀረበለትን ባለሙያና የሥራ ሂደት አስተባባሪን ጠርቶ ማነጋገርና ማወያየት ይችላል።
- ✓ ታክስ ከፋዩ ጥያቄ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ በጥያቄው ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት።
- ✓ የቅ/ጽ/ቤቱ ስህተት አለመኖሩን ውሳኔ ከሰጠና ታክስ ከፋዩ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው ውሳኔው በደረሰው በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለዋና መ/ቤቱ (ም/ዴኤታ) ማቅረብ ይኖርበታል።

የታክስ ስሌት ስህተትን ስለማረም...

- ✓ በቅሬታው ላይ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።
- ✓ በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ውሳኔው በደረሰው በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለሚኒስትሩ በጽ/ቤቱ በኩል ያቀርባል።
- ✓ ጥያቄው በቀረበ በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ጽ/ቤት በኩል የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።
- ✓ ስህተቱ እንዲታረም ከተወሰነ፣ የመጀመሪያ ውሳኔ በሰጠው የሥራ ክፍል በኩል የተስተካከለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ይሰጣል።

ሙከራ ሁለት

የስሌት ስህተቶች የሚታረሙበትን መንገድ ግለጹ?

2.2.6. የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብዓት ስለማቀናነስ

- በግምት የተወሰነው የምርት ገቢ በቀጥታ ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት የዋለ አቅርቦ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ግብይት የተከናወነበትን ጊዜ መሠረት በማድረግ በጊዜው ያሳወቀው እና ለአቅርቦት በታክስ ደረሰኝ/ዲክላራሲዮን መሠረት የተከፈለው ተ.እ.ታ. ከግብዓት ታክሱ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል።

- በሒሳብ መዝገብ ተቀባይነት ያላገኘው የግብዓት ታክስ የተጠየቀበት ማስረጃ ግብይት የተፈፀመበት ስለመሆኑ አጠራጣሪና ማረጋገጥ የማይቻል ወይም ከሁለተኛ ደረሰኝ ጋር የተገናኘ ከሆነ የግብዓት ታክሱ አይቀናነስም።

የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብዓት ስለማቀናነስ...

- ታክስ ከፋዩ የዘመኑን የሒሳብ መግለጫ አቅርቦ ኦዲት ሲደረግ በባለሥልጣኑ በተደረገ ክትትል በተደጋጋሚ ደረሰኝ የማይሰጥ ወይም የሽ.መ.መ. የማይጠቀም መሆኑ ተረጋግጦ ገቢው በግምት የተወሰነ እንደሆነ በወርሃዊ የ.እ.ታ. ማስታወቂያ የገለጸው የግብዓት ታክስ ተቀናሽ ይደረጋል።

2.2.8. የማኑዋል ደረሰኝ ሲጠፋ ስለሚኖረው አሠራር

- ታክስ ከፋዩ ምንም ያልተሠራበት ደረሰኝ የጠፋበት መሆኑን ያስታወቀ እንደሆነ ባለሥልጣኑ በሌላ መንገድ ደረሰኝ የጠፋበት መሆኑን ባስታወቀው ታክስ ከፋይ ስለመሠራቱ የሚገልጽ መረጃ ካላገኘ በስተቀር ታክስ አይወሰንበትም።

- የጠፋበትን ማንዋል ደረሰኝ ለባለሥልጣኑ ስለመጥፋቱ ሲያሳውቅ የሚከተሉትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ ታክሱ ይወሰናል፤

  - ✓ የጠፋው ደረሰኝ በከፊል የተሠራበት ከሆነ ቀሪ ካለው ከቀሪው ላይ የሚገኝ መረጃ፣ ወይም ቀሪ ከሌለው ታክስ ከፋዩ የተሠማራበት የንግድ ዘርፍ ባህሪ ከገዥዎቹ መረጃ የሚኝበት ሲሆን ከገዥዎች የተገኘውን መረጃ፣ ወይም

የማኑዋል ደረሰኝ ሲጠፋ ስለሚኖረው አሠራር...

- ✓ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርባቸው ዕቃዎች ተመሳሳይ ዋጋና ደረጃ ያላቸው ሲሆኑ በቆጠራ የተሸጠውን ዕቃ ብዛት በመለየት የሽያጭ ደረሰኝ የጠፋባቸውን ዕቃዎችን የሽያጭ ደረሰኝ ባላቸው ዋጋ እንደተሸጡ ተቆጥሮ በማባዛት የሚገኝ ይሆናል።

- ✓ የሽያጭ መረጃ ለማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ የታክስ ከፋዩ ዕቃ ወይም አገልግሎት ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መሠረት ታክሱ በግምት የሚወሰን ይሆናል።

- ✓ የጠፋው ደረሰኝ ሙሉ ለሙሉ የተሠራበት ደረሰኝ ከሆነ የሚወክለውን ሽያጭ መጠን ለማግኘት ከላይ የተገለጹትን መንገዶች በመከተል ታክሱ ይወሰናል።

የማኑዋል ደረሰኝ ሲጠፋ ስለሚኖረው አሠራር...

- ታክስ ከፋዩ ምንም ያልተሠራበት ደረሰኝ የጠፋበት መሆኑን ሳያስታውቅ ባለሥልጣኑ በምርመራ ሂደት የደረሰበት እንደሆነ የተሠራበት ደረሰኝ እንደጠፋ ተቆጥሮ በተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ወቅት፣ ንግድ እና አካባቢ የሚገኝ የሦስት ታክስ ከፋይ ያስታወቀውን ወይንም የተወሰነበትን አማካይ ሽያጭ መሠረት በማድረግ ታክሱን በግምት ይወስናል።

2.3 የስጋት የታክስ ስሌት /27/

“የስጋት የታክስ ስሌት”:-ማለት ባለሥልጣኑ ከስጋት በመነሳት የሚያከናውነው የታክስ ስሌት ነው።

ባለሥልጣኑ በአንድ የታክስ ጊዜ ማንኛውም ታክስ ከፋይ መክፈል ለሚገባው ታክስ በሚያገኘው ማስረጃ ላይ በመመሥረት የስጋት ታክስ ስሌት ሊያዘጋጅ ይችላል። ይህ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው ታክስ ከፋዩ ለታክስ ጊዜው የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ እንደሆነ እና ታክሱ በታክስ ስሌት የሚሰበሰብ ሲሆን ብቻ ነው።

የስጋት የታክስ ስሌት.....

- ባለሥልጣኑ፤ የስጋት ታክስ ስሌት ለተዘጋጀለት ታክስ ከፋይ የሚከተሉትን ዝርዝር ነጥቦች ያካተተ የስጋት ታክስ ስሌት ማስታወቂያ በጽሑፍ መስጠት አለበት፦
  - ✓ የተሰላውን የታክስ መጠን፤
  - ✓ በተሰላው የታክስ መጠን ላይ የሚከፈል ቅጣት ካለ፤
  - ✓ የታክስ ስሌቱ የሚመለከተውን የታክስ ጊዜ፤
  - ✓ ታክሱና ቅጣቱ የሚከፈልበትን ጊዜ፣ይህ ጊዜ የታክሱ የመክፈያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ሊሆን ይችላል፤

የስጋት የታክስ ስሌት.....

- ✓ ቅሬታ ማቅረብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ጨምሮ በስጋት ታክስ ስሌቱ ላይ ቅሬታውን የሚያቀርብበትን አኳኋን።

- ➢ ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ በሚሰጠው የስጋት ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ታክሱ እና ቅጣቱ ወዲያውኑ እንዲከፈል ሊያዝ ይችላል።

- ➢ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀ የስጋት ታክስ ስሌት የደረሰው ማንኛውም ታክስ ከፋይ የስጋት ታክስ ስሌቱ የሚመለከተውን የታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታውን አያስቀርም።

- ➢ የስጋት ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከደረሰው በኋላ ለዚያ የታክስ ጊዜ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የታክስ ማስታወቂያ ለታክስ ጊዜው እንደቀረበ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ አይቆጠርም።

የስጋት ታክስ ስሌትን በማምት ስለመወሰን ሙ/138/2010

- ባለሥልጣኑ ቀጥሎ በተመለከተው መንገድ የስጋት ታክስ ስሌትን በግምት ሊወሰን ይችላል፤

✓ ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩ ታክስ የመክፈል ሁኔታው ስጋት ላይ የሚጥል ማስረጃ ሲያጋጥምና ታክሱን በሒሳብ መዝገብ መሠረት መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ የስጋት ስሌትን በግምት ግብር አወሳሰን ሥርዓት ይወስናል።

✓ ይህ የሚሆነው የሠንጠረዥ "ለ" እና "ሐ" ገቢ በሚያገኝ ታክስ ከፋይ ላይ ብቻ ይሆናል።

✓ የሚወሰነው የግምት የስጋት ታክስ ስሌት እንደ አግባብነቱ የተርን ኦቨር ታክስ ወይም የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰላበት ይሆናል።

2.4. የተሻሻሉ የታክስ ስሌቶች

ባለሥልጣኑ፡-

- የታክስ ከፋዩ በሠንጠረዥ “ለ” ወይም “ሐ”ን በተመለከተ ኪሳራ ለታክስ ጊዜው በትክክል የተሰላ መሆኑን
- ታክስ ከፋዩ በታክስ ጊዜው በብልጫ የከፈለው የግብዓት ተጨማሪ እሴት ታክስ በትክክል የተሰላ መሆኑን፤
- ታክስ ከፋዩ ዜሮ መጠንን ጨምሮ ለታክስ ጊዜው መክፈል የሚገባው የታክስ መጠን በትክክል የተሰላ መሆኑን፣ ለማረጋገጥ በሚያገኘው ማስረጃ መሠረት ማንኛውንም የታክስ ስሌት በመለወጥ፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር ሊያሻሽል ይችላል።

የተሻሻሉ የታክስ ስሌቶች .....

- አግባብነት ባለው የታክስ ሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር፣ባለሥልጣኑ ማንኛውንም የታክስ ስሌት፦
  - ✓ በማንኛውም ጊዜ በታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ ከፋዩ ስም የማጭበርበር ድርጊት ሲፈጸም ወይም በከፍተኛ ሁኔታ ወይም በማወቅ የተፈፀመ የቸልተኝነት ድርጊት ሲኖር፤ ወይም

የተሻሻሉ የታክስ ስሌቶች .....

- ✓ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ፦
  - ታክስ ከፋዩ በራሱ የሚያሰላው የታክስ ስሌት ሲሆን ታክስ ከፋዩ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያውን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 5 (አምስት) ዓመት ውስጥ፤
  - ለሌላ ማንኛውም የታክስ ስሌት ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 5(አምስት) ዓመት ውስጥ፤ ሊያሻሽል ይችላል።

- ባለሥልጣኑ የተሻሻለውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከሰጠው በኋላ ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ በማናቸውም ሁኔታ ባለሥልጣኑ የሚያደርገው ተጨማሪ ማሻሻያ መጀመሪያ በተሻሻለው የታክስ ስሌት ላይ በተደረጉት ለውጦች፣ ቅናሾች ወይም ጭማሪዎች ላይ ብቻ የተገደበ ይሆናል።

- ባለሥልጣኑ በዚህ መሠረት የተሻሻለውን የታክስ ስሌት በተመለከተ የሚከተሉትን ነጥቦች ያካተተ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ መስጠት አለበት፦
  - ✓ ማሻሻያ የተደረገበትን የመጀመሪያ የታክስ ስሌት እና ማሻሻያ ማድረግ ያስፈለገበትን ምክንያቶች የያዘ መግለጫ፤

- ✓ እንደሁኔታው የተሰላውን የታክስ መጠን፣ ወደ ፊት የሚሸጋገር የኪሣራ ወይም በብልጫ የተከፈለን የግብዓት ታክስ መጠን፤
- ✓ በተሻሻለ የታክስ ስሌት ላይ ሊከፈል የሚገባ የቅጣት መጠን ካለ፤ በተሻሻለው የታክስ ስሌት ላይ ሊከፈል የሚገባ የዘገየ ክፍያ ወለድ መጠን ካለ፤
- ✓ የተሻሻለው የታክስ ስሌት የሚመለከተውን የታክስ ጊዜ፤
- ✓ ማስታወቂያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ከ30 (ከሰላሳ) ቀናት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ በተሻሻለው የታክስ ስሌት መሠረት መከፈል ያለበትን ተጨማሪ ታክስ፣ ቅጣት እና ወለድ የሚከፈልበትን ቀን፤
- ✓ ቅሬታ ማቅረብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ጨምሮ በተሻሻለው የታክስ ስሌት ላይ ቅሬታውን የሚያቀርብበትን አካኋን።

የተሻሻሉ የታክስ ስሌቶች...

- በተሻሻለው የታክስ ስሌት መሠረት መከፈል ያለበት ተጨማሪ ታክስ ካለ በተጨማሪው ታክስ ላይ ለዘገየ ክፍያ የሚከፈል ቅጣትና ወለድ የሚሰላው በመጀመሪያው የታክስ ስሌት መሠረት ታክሱ መከፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ ነው።

የግምት ታክስ ስሌት ስለማሻሻል መ/138/2010

የግምት ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከተሰጠ በኋላ የግዥ/የሽያጭ መጨመርን የሚሳይ መረጃ ከተገኘ፤ የመጀመሪያ የግምት ስሌት ውሳኔ በተሳሳተ መረጃ ላይ የተመሠረተ መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሻሻለው የግምት ስሌት ለ2ኛ ጊዜ ይሻሻላል።

የግምት ታክስ ስሌት ስለማሻሻል.....

- የግምት ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከተሰጠ በኋላ የግዥ ወይም የሽያጭ መጨመርን የሚሳይ መረጃ የተገኘ እንደሆነ፣
- የመጀመሪያ የግምት ስሌት ውሳኔ በተጭበረበረ ወይም በተሳሳተ መረጃ ላይ የተመሠረተ መሆኑ ሲረጋገጥ፣
- ለመጀመሪያ ጊዜ የተሻሻለው የግምት ታክስ ስሌት ለሁለተኛ ጊዜ ሊሻሻል የሚችለው ከላይ የተገለጹ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ነው።

2.5. የታክስ ስሌቶችን ስለማስፈጸም /38 /

- በታክስ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ የውሳኔው ማስታወቂያ በደረሰው በ21 ቀናት ውስጥ ቅሬታ ካላቀረበ ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ የሚሰጠው የታክስ ስሌት የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜው ካበቃበት ቀን ጀምሮ የመጨረሻ እና ተፈፃሚነት ያለው ይሆናል።
- ታክስ ከፋዩ በታክስ ስሌቱ ላይ ቅሬታ ካቀረበ፣የታክስ ስሌቱ ከሚከተሉት የዘገየው ሁኔታ በተፈፀመበት ጊዜ የመጨረሻ ይሆናል:-
  - ✓ ታክስ ከፋዩ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በታክስ ስሌቱ ላይ ይግባኝ ካላቀረበ፣ይግባኝ በሚባልበት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የፈለገ ሰው የውሳኔ ማስታወቂያው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ የፀደቀውን

ስሌቶችን ስለማስፈጸም...

ቅጽ በመጠቀም በውሳኔው ላይ የይግባኝ ማመልከቻ ለኮሚሽኑ ማቅረብ የሚችል ሲሆን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ሲጠናቀቅ፤

- ✓ ታክስ ከፋዩ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በታክስ ስሌቱ ላይ ይግባኝ ካቀረበ፣ ለኮሚሽኑ በቀረበ የታክስ ይግባኝ ተካፋይ የነበረ ሰው ኮሚሽኑ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ የኮሚሽኑ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 /ሠላሳ/ ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማስታወቂያውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ የሚችል ሲሆን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚቀርብበት ጊዜ ሲጠናቀቅ፤

ስሌቶችን ስለማስፈጸም...

- ✓ ታክስ ከፋዩ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በታክስ ስሌቱ ላይ ይግባኝ ካቀረበ፣ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀረበ የታክስ ይግባኝ ተካፋይ የነበረ ሰው ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ የፍርድ ቤቱ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 /ሠላሳ/ ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማስታወቂያውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ የሚችል ሲሆን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚቀርብበት ጊዜ ሲጠናቀቅ፤ ወይም
- ✓ ታክስ ከፋዩ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በታክስ ስሌቱ ላይ ይግባኝ ካቀረበ፣ ፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ።

ስሌቶችን ስለማስፈጸም...

- በክርክር ላይ ያለን ታክስ በስሌት ላይ ከቀረበ ቅሬታ ጋር በተገናኘ በታክስ ከፋይ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የሚቀርብ የይግባኝ ማስታወቂያ በአግባቡ ቀርቧል ሊባል የሚችለው በክርክር ላይ ያለ ታክስ 50 በመቶ የተከፈለ እንደሆነ ብቻ ነው።
- በታክስ ስሌት ላይ ከቀረበ ቅሬታ ጋር በተገኛኘ በታክስ ከፋይ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብ የይግባኝ ማስታወቂያ በአግባቡ ቀርቧል ሊባል የሚችለው በክርክር ላይ ያለ ታክስ 75 በመቶ የተከፈለ እንደሆነ ብቻ በመሆኑ ከመክፈል አይከለክልም።
- የመጨረሻ በሆነ የታክስ ስሌት የሚፈለግበትን ታክስ መሠረት ያልከፈለ ታክስ ከፋይ ግዴታውን ያልተወጣ የታክስ ባለዕዳ ይሆናል።

ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመሰብሰብ እና ማስከፈል

3.1. ታክስ ለመንግሥት የሚከፈል ዕዳ ስለመሆኑ /30/

- በታክስ ሕግ መሠረት በታክስ ከፋዩ ሊከፈል የሚገባው እና የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ታክስ ለመንግሥት የሚከፈል ዕዳ ስለሆነ ለባለሥልጣኑ መከፈል አለበት።



3.2. በሁለተኛ ደረጃ የሚመጡ ኃላፊነቶች እና ታክሰን ለማስከፈል የሚደረጉ ወጪዎች

- ባለሥልጣኑ የሁለተኛ ደረጃ ኃላፊነት ላለበት ወይም ታክሰን ለማስከፈል የተደረገን ወጪ መክፈል ላለበት ማንኛውም ሰው መክፈል ያለበትን የገንዘብ መጠን እና ክፍያው የሚፈጸምበትን ቀን የሚገልጽ ማስታወቂያ ይሰጣል።
- የሁለተኛ ደረጃ ኃላፊነት ባለበት ሰው የተከፈለ ታክስ ይኸው ኃላፊነት ከሚመለከተው የታክስ ከፋዩ የመጀመሪያ የታክስ ኃላፊነት ጋር ይካካሳል።

3.3. የታክስ መክፈያ ጊዜን ስለማራዘም /32/

- የመክፈያ ጊዜው እንዲራዘምለት ለባለሥልጣኑ የጽሑፍ ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ ባለሥልጣኑ በቂ ምክንያት መኖሩን ካረጋገጠ የታክስ ከፋዩ የታክስ መክፈያ ጊዜውን ሊያራዝምለት፤ ወይም ባለሥልጣኑ ታክሱን በመከፋፈል በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል ሊያደርገው ይችላል።
- ይህ የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ በዘገየው ክፍያ ላይ ከመጀመሪያ የታክስ መክፈያ ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ወለድ የመክፈል ግዴታውን አያስቀርም።
- በቀረበ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ማመልከቻ ላይ የታክስ ባለሥልጣኑ የሰጠውን ውሳኔ የሚገልፅ የጽሑፍ ማስታወቂያ ማመልከቻው በቀረበ በ30 ቀናት ውስጥ ይሰጣል።

የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች

- ታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳውን በአንድ ጊዜ መክፈል የማይችል ሲሆን፣
- ታክስ ከፋዩ በታክስ ማስታወቂያ በደረሰው ጊዜ በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ውስጥ የማይገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ።
- በከፍተኛ የሥጋት ደረጃ የተለየ፣ ሀብት በዕዳ የተያዘበት ወይም ንብረት እንዲሸጥ ጨረታ የወጣበት ታክስ ከፋዩ ዕዳውን ለመክፈል ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ለዕዳው ተመጣጣኝ የሆነ የባንክ ዋስትና ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል።

የታክስ መክፈያ ጊዜን ስለማራዘም.....

የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች

- በታክስ ማስታወቂያ ጊዜ መከፈል ያለበት የታክስ ዕዳ ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ ወይም ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ መደረግ ያለበት ሲሆን፣
- አስቀድሞ የክፍያ ጊዜ ስምምነት የተሰጠው ሆኖ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት ዕዳውን ያልከፈለ፣
- የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተጠየቀበት የታክስ ዕዳ መጠን እንደ ታክስ ከፋዩ አመዳደብ ከተቀመጠው አነስተኛ የገንዘብ መጠን በታች ከሆነ፣

የታክስ መክፈያ ጊዜን ስለማራዘም.....

- በታክስ ዘመኑ በከፍተኛ የሥጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ ከሆነ፣
- ለዕዳው ማስከፈያ ሃብት እና ንብረት የተያዘበት ከሆነ፣ በዕዳ የተያዘበትን ንብረት ለመሸጥ የጨረታ ማስታወቂያ የወጣበት ከሆነ፣ የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የሚሰጠው ለዕዳው ተመጣጣኝ የሆነ የባንክ ዋስትና ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል።

3.3.1. የክፍያ ጊዜ ስምምነት ስለሚፈቅደው አካል እና የጊዜ ገደብ ስለመወሰን

- ታክስ ከፋዩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ራሱ አስታውቆ የሚከፍለውን የንግድ ትርፍ ግብር መክፈል አለመቻሉን ጠቅሶ ሲያመለክት ጥያቄውን የቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ አሳማኝ ምክንያት መሆኑን ሲያረጋግጥ ከ3 ወር ላልበለጠ ጊዜ እንዲራዘምለት ሊፈቅድ ይችላል።

- ይህ ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ለ3 የግብር ዘመን ተመሳሳይ ጥያቄ የሚያቀርብ ከሆነ የታክስ ዕዳ መክፈያ ጊዜ አይራዘምለትም።

የክፍያ ጊዜ ስምምነት ስለሚፈቅደው.....

የታክስ ዕዳ የመክፈያ ጊዜ ስለመወሰን

- በከፍተኛ ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ጠቅላላ ዋና ታክስ፣ መቀጫ እና ወለድ ዕዳ:-
  - ✓ ከብር 750 ሺ-25ዐ ሺ ከሆነ እስከ 6 ወር
  - ✓ ከብር 2 ሚሊዮን 5 መቶ ሺ አንድ-ብር 3 ሚሊዮን 75ዐ ሺ ከሆነ እስከ 8 ወር፣
  - ✓ ከብር 3 ሚሊዮን 75ዐ ሺ አንድ እስከ 5 ሚሊዮን ከሆነ እስከ 1ዐ ወር፣
  - ✓ ከብር 5 ሚሊዮን በላይ ከሆነ እስከ 12 ወር የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

የታክስ ዕዳ የመክፈያ ጊዜ ስለመወሰን...

- በመካከለኛ ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ዋና ታክስ፣ መቀጫና ወለድ ዕዳ:-

- ✓ ከብር 5ዐ ሺ- ብር 125 ሺ ከሆነ 3 ወር፣
- ✓ ከብር 125 ሺ አንድ እስከ 75ዐ ሺ/ ከሆነ እስከ 6 ወር፣
- ✓ ከብር 75ዐ ሺ አንድ እስከ 2 ሚሊዮን 5ዐዐ ሺ ከሆነ እስከ 8 ወር፣
- ✓ ከብር 2 ሚሊዮን 5ዐዐ ሺ አንድ እስከ ብር 3 ሚሊዮን 75ዐ ሺ ከሆነ እስከ 1ዐ ወር፣
- ✓ ከብር 3 ሚሊዮን 75ዐ ሺ በላይ ከሆነ 12 ወር፣ የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

የታክስ ዕዳ የመክፈያ ጊዜ ስለመወሰን...

- በአነስተኛ ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ጠቅላላ ዋና ታክስ፣መቀጫ እና የወለድ ዕዳ:-
  - ✓ ከብር 5 ሺ እስከ 12 ሺ 5ዐዐ ከሆነ እስከ 3 ወር፣
  - ✓ ከብር 125 ሺ አንድ- ብር 75 ሺህ ከሆነ እስከ 6 ወር፣
  - ✓ ከብር 75 ሺ አንድ-ብር 25ዐ ሺ ከሆነ እስከ 8 ወር፣
  - ✓ ከብር 25ዐ ሺ አንድ-75ዐ ሺ ከሆነ እስከ 1ዐ ወር፣
  - ✓ ከብር 75ዐ ሺ በላይ ከሆነ እስከ 12 የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

የታክስ ዕዳ የመክፈያ ጊዜ ስለመወሰን...

- በጥቃቅን ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ጠቅላላ ዋና ታክስ፣ መቀጫ እና ወለድ ዕዳ:-

  - ✓ ከብር 1 ሺ እስከ 10 ሺ ከሆነ እስከ 3 ወር፣
  - ✓ ከብር 1 ሺ አንድ-20 ሺ ከሆነ እስከ 6 ወር፣
  - ✓ ከብር 20 ሺ አንድ-40 ሺ ከሆነ እስከ 8 ወር፣
  - ✓ ከብር 40 ሺ አንድ እስከ 60 ሺ ከሆነ እስከ 10 ወር፣
  - ✓ ከብር 60 ሺ አንድ በላይ ከሆነ እስከ 12 ወር የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

የታክስ ዕዳ የመክፈያ ጊዜ ስለመወሰን.....

- የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተሰጠው ታክስ ከፋይ ከታክስ ባለሥልጣኑ ጋር የክፍያ ጊዜ ስምምነት እንዲፈርም ይደረጋል።
- የታክስ ዕዳ የመክፈያ ጊዜ እንዲራዘም የቀረበለት የሥራ ኃላፊ ማስረጃውን በመመዘን በከፍተኛ ታክስ ከፋዮች፣ በመካከለኛ ግብር ከፋዮች፣በአነስተኛ ግብር ከፋዮች እና በጥቃቅን ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በተመለከተው የመክፈያ ጊዜ አሰጣጥ ሥርዓት መሠረት ዕዳውን እንዲከፍል በድጋሚ ሊፈቅድለት ይችላል። ሆኖም ግን ድጋሚ ተፈቅዶለት ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ ሌላ የታክስ ማራዘሚያ ስምምነት ሊፈቀድለት አይቻልም።

3.3.2 የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ እንዲፈቀድለት የሚጠይቅ ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

- የክፍያ ጊዜ ስምምነት በሚገባባቸው ዕዳዎች 25%ቅድሚያ መክፈል አለበት።
- የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ የቀረበው ሀብት ከተያዘ በኋላ ሲሆን የታክስ ባለሥልጣኑ ጉዳዩን ለማስፈጸም ያወጣውን ወጪዎችን እና ቢያንስ የታክስ ዕዳውን 25% ቅድሚያ ይከፈላል።
- ለታክስ ዕዳ ሀብት የተያዘበት የታክስ ከፋይ ዕገዳው ሊነሳለት የሚችለው ለዕዳው ተመጣጣኝ የሆነ የባንክ ዋስትና ሲያቀርብ ብቻ ነው።

3.3.3. በልዩ ሁኔታ የሚሰጥ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ

- በልዩ ሁኔታ የመክፈያ ጊዜ እንዲራዘም የሚቀርቡ ጥያቄዎች የሚቀርቡት ለቅ/ጽ/ቤቱ ይሆናል።
- ቅ/ጽ/ቤቱ ስለ ታክስ ከፋዩ የታክስ አከፋፈል ታሪክና በልዩ ሁኔታ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተጠየቀበትን ምክንያት አጣርቶ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ይልካል።
- የታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬቱ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስትሩ ወይም ለወከለው የሥራ ኃላፊ አቅርቦ በሚወሰነው መሠረት እንዲፈፀም ለቅ/ጽ/ቤቱ መልሶ ያስተላልፋል።

በልዩ ሁኔታ የሚሰጥ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ...

- ሚኒስትሩ ወይም በእርሳቸው የተወከለው የሥራ ኃላፊ የክፍያ ስምምነት ለገባ ታክስ ከፋይ ያለበትን የእዳ ጫና ከግምት ውስጥ በማስገባት የቅድሚያ ክፍያውን እስከ 15 በመቶ ዝቅ ሊያደርግ ይችላል።
- የአዲስ አበባና ድሬዳዋ አስተዳደር ገቢዎች ባለሥልጣንን በተመለከተ በተመሳሳይ ደረጃ ባሉ ኃላፊዎች ይከናወናል።

3.3.4. የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ አቀራረብ፤ ስለሚፈቅደው አካል እና አፈፃፀም ሥርዓት

- የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በአንዴ የመክፈል አቅም የሌለው መሆኑን ገልጾ ጥያቄውን ለቅ/ጽ/ቤቱ የታክስ ዕዳ አስተዳደር ሥራ ሂደት ሲያቀርብ እና ምክንያቱ ተቀባይነት ሲያገኝ የሚስተናገድ ይሆናል።
- ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረበ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ከሆነ የታክስ ዕዳ አስተዳደር ሥራ ሂደት አስተባባሪ ሊፈቅድ ይችላል።
- በድጋሚ የቀረበ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ከሆነ የታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ የሚፈቅድ ይሆናል።

የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ አቀራረብ፣.....

- ታክስ ከፋዩ ያቀረበው የታክስ ዕዳ አስተዳደር ባለሙያ የስምምነት ውል በማዘጋጀት ለሥራ ሂደት መሪው አቅርቦ እንዲፈረም ያደርጋል።
- የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል በ3 ኮፒ ተዘጋጅቶ ዋናው ኮፒ ከማህደር ጋር ይያያዛል፣ 2ኛው ኮፒ ለግብር ከፋዩ ይሰጣል፣ 3ኛው ኮፒ በታክስ ዕዳ ክትትል ሥራ ሂደት ለቀጣይ የክትትል ሥራ የሚያዝ ይሆናል።
- በክፍያ ጊዜ ስምምነት ውሉ መሠረት ክፍያ የሚፈጸምበት ቀን በበዓላት ወይም በእረፍት ቀናት ላይ ከዋለ ክፍያው በቀጣዩ የሥራ ቀን ይሆናል። ጸጉሜ የነሐሴ ወር አካል ሆኖ ይቆጠራል።

3.3.5. የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል ግዴታን አለመፈጸም

- የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ በውሉ መሠረት በየወሩ ካልከፈለ ታክስ ከፋዩ ክፍያውን ካቆመበት ጊዜ አንስቶ ያልተከፈለውን ቀሪ ክፍያ እና ቀሪ መቀጫ ተሰልቶ በሙሉ እንዲከፍል በታክስ ባለሥልጣኑ የዕዳ አሰባሰብ የሥራ ክፍል በታክስ ሕጉ መሠረት እርምጃ ሊወስድ ይችላል።
- ክፍያ ያቋረጠው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ ከተረጋገጠ አቋርጦት የነበረውን ታክስ በስምምነት ውል ጊዜ ውስጥ ያልከፈለውን ወራት አጠቃሎ እና የወጡ ወጪዎችን ጨምሮ የከፈለ ከሆነ የስምምነቱ ውል ሳይሰረዝ እንዲቀጥል ይደረጋል።

3.4. ታክስ እና ለሶስተኛ ወገን በሚሰጥ የክፍያ ትዕዛዝ በሚከፈል ገንዘብ ላይ ስለሚኖር የቅድሚያ መብት /33 /

- በታክስ እና ለሶስተኛ ወገን በሚሰጥ የክፍያ ትዕዛዝ በሚከፈል ገንዘብ ላይ የሚኖር የቅድሚያ መብት ለሚከተሉት ክፍያዎች ተፈጻሚነት ይኖረዋል:-
  - ✓ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ በሚከፈል ታክስ፤ በተጨማሪ እሴት ታክስ፤ በተርን ኦቨር ታክስ ወይም በኤክሳይዝ ታክስ እና
  - ✓ ለሦስተኛ ወገን በሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ መሠረት ሊከፈል በሚገባው ገንዘብ ላይ ይሆናል።

ታክስ እና ለሶስተኛ ወገን በሚሰጥ የክፍያ ትዕዛዝ.....

- ይህ ተፈጻሚ በሚሆንበት ገንዘብ ባለዕዳ የሆነ፣ የያዘ፣የተረከበ ወይም ቀንሶ የሚያስቀር ሰው ይህንን ገንዘብ የመንግሥት ባለአደራ በመሆን የሚይዝ ስለሆነ ይህ ሰው ሊከስር ወይም ንብረቱ ሲጣራ የመንግሥት ባለአደራ በመሆን የያዘው ገንዘብ:-
  - ✓ በንብረት ማጣራቱ ሂደት ወይም በኪሳራው የጠቅላላ ንብረቱ አካል ተደርጎ አይወሰድም፤ እንዲሁም
  - ✓ ምንም ዓይነት የንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት ለባለሥልጣኑ መከፈል አለበት።

ታክስ እና ለሶስተኛ ወገን በሚሰጥ የክፍያ ትዕዛዝ.....

- በሌላ ማንኛውም ዓይነት ሕግ በተለየ አኳኋን የተደነገገ ቢኖርም ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ታክስ:-
  - ✓ ከማንኛውም ሰው ለሚፈልግ ማንኛውም ዕዳ ወይም ኃላፊነት ማስፈጸሚያ ሊከበር አይችልም፤
  - ✓ ታክሱ ተይዞ ቀሪ ከሚደረግበት ክፍያ ላያ ከሚፈለጉ ዕዳዎች ሁሉ የመጀመሪያ ይሆናል፤ እንዲሁም
  - ✓ በማንኛውም ሕግ ወይም የፍርድ ትዕዛዝ መሠረት ከክፍያው ላይ ከሚቀነስ ማንኛውም የገንዘብ ክፍያ ቅድሚያ ይኖረዋል።

3.5. የታክስ ዕዳ አከፋፈል ቅደም ተከተል የማስቀመጥ

- አንድ ታክስ ከፋይ የታክስ ግዴታውን በወቅቱ ባለመክፈሉ ምክንያት ቅጣት እና ወለድ መክፈል በሚኖርበት ጊዜ የአከፋፈል ቅደም ተከተሉ:-
  - ✓ በመጀመሪያ ዋና ዕዳ፣
  - ✓ በሁለተኛ ደረጃ ወለዱ፣
  - ✓ በመጨረሻ ቀሪው ለቅጣት ይሆናል።
- ማንኛውም ታክስ ከፋይ ክፍያ በሚፈፀምበት ጊዜ ከአንድ በላይ የታክስ ዕዳ የሚፈለግበት ከሆነ ክፍያው የሚሸፍነው ዕዳ ቅደም ተከተል ዕዳው በተፈጠረበት ጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት ይሆናል።

- ባለሥልጣኑ የመንግሥትን ገቢ ለመጠበቅ አስፈላጊ መስሎ ሲታየው አስፈላጊ ነው በሚለው መጠንና አኳኋን ታክስ ከፋዩ ዋስትና እንዲያቀርብ ሊያስገድደው ይችላል።
- ታክስ ከፋዩ ዋስትና እንዲያቀርብ የሚጠየቀው:-
  - ✓ የመክፈያ ጊዜው ለደረሰ/ለሚደርስ ታክስ መክፈያ፤ ወይም
  - ✓ ተመላሽ ለሚጠይቅ ታክስ ከፋይ ቅድመ-ሁኔታ ይሆናል።
- የሚሰጠው ዋስትና ባለሥልጣኑ የሚጠይቃቸው ተገቢ ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ ዋስትና ሊሰጥ ይችላል። ታክስ ከፋዩ ዋስትና ማቅረብ ግዴታ የሚኖርበት ባለሥልጣኑ:-
  - ✓ የሚፈለገው የዋስትና መጠን፣
  - ✓ ዋስትው የሚቀርብበትን አኳኋን እና
  - ✓ ዋስትናው የሚቀርብበትን ቀን የሚገልፅ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ የሰጠ እንደሆነ ብቻ ነው።

3.7 ስለጥበቃ /36/

ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ታክስ ቀንሶ ለባለሥልጣኑ የከፈለ ሰው፤ ለባለሥልጣኑ ታክስ የከፈለ የታክስ እንደራሴ፤ ለባለሥልጣኑ ታክስ የከፈለ ተረካቢ፤ ወይም ለሶስተኛ ወገን በሚሰጥ የክፍያ ትዕዛዝ መሠረት ለባለሥልጣኑ ገንዘብ ከፈለ ሰው ታክስ ከፋዩን በመወከል በታክስ ሕግ መሠረት ለባለሥልጣኑ የከፈለውን ገንዘብ እንዲከፍል ክስ ሊቀርብበት አይችልም።

3.8. ለዘገየ ክፍያ የሚከፈል ወለድ /37/

- በታክስ መክፈያ ጊዜው ወይም ከዚያ በፊት ታክሱን ያልከፈለ ታክስ ከፋይ በየሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ በዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ መጣኔ ላይ 15 በመቶ ተጨምሮበት ታክሱ መክፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ እስካለለቀበት ቀን ድረስ ባልተከፈለው መጠን ላይ ለዘገየው ክፍያ ወለድ የመክፈል ግዴታ አለበት።

ለምሳሌ ፡- በ2014 የንግድ ባንኮች ማበደሪያ ወለድ 18 በመቶ ቢሆን 15 በመቶ ተጨምሮበት 20.7% ታክሱ መክፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ወለድ የመክፈል ግዴታ አለበት ።

- በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ ታክስን በመክፈያ ጊዜው ባለመክፈል ከሚጣለው ቅጣት በተጨማሪ ይሆናል።

ለዘገየ ክፍያ የሚከፈል ወለድ...

- ወለዱ በነጠላ ወለድ በየቀኑ ይሆናል።
- ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ መክፈል ያለበትን የወለድ መጠንና የመክፈያ ጊዜውን የሚገልጽ ማስታወቂያ ይሰጠዋል።
- ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ በሚከፈል ታክስ/በ2ኛ ደረጃ ኃላፊነት በሚከፈል ታክስ ላይ የሚታሰብ የዘገየ ክፍያ ወለድ መክፈል ያለበት ይኸው ኃላፊነት ባለበት ሰው ብቻ ነው።
- በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ ጠቅላላ መጠን ከታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳ ሊበልጥ አይችልም።

3.9. በሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት ጥያቄ

/39/

- ማንኛውም ቀዳሚ ዋስትና የተሰጠበት መብት እንደተጠበቁ ሆነው የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ታክስ በሙሉ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ባለሥልጣኑ በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ የቀደምትነት መብት ይኖረዋል።

- ቀዳሚ ዋስትና የተሰጠበት መብት ባንኮች ዋስትና የተቀበሉባቸው የገንዘብ ጥያቄዎችና የተቀጣሪዎችን የደመወዝ የቅድሚያ መብት ይጨምራል። ሆኖም ከተከፋይ ሒሣብ ላይ ተቀንሶ በሚከፈል ታክስ፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ፣ በተርን ኦቨር ታክስ፣ ወይም በኤክሳይዝ ታክስ ጋር በተገናኘ ተፈጻሚ አይሆንም።

በሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት ጥያቄ...

- በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ የባለሥልጣኑን የዋስትና መብት እንዲመዘግብ ንብረቱን ለመዘገበው አካል እንደሚያመለክት የሚገልጽ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ይሰጣል።

- ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ ማስታወቂያው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ፣ ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ በሰጠው ማስታወቂያ የተመለከተው የታክስ ከፋዩ ሀብት ላልተከፈለው ታክስ እና ታክሱን ለማስከፈል ለሚደረግ ወጪ በዋስትና እንዲያዝ ንብረቱን ለመዘገበው አካል የጽሑፍ ትዕዛዝ ይሰጣል።

በሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት ጥያቄ...

- ባለሥልጣኑ ሀብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ መዝጋቢው ባለሥልጣን ሀብቱ በዋስትና እንዲያዝ የደረሰውን የጽሑፍ ትዕዛዝ ምንም ዓይነት ክፍያ ሳይጠይቅ እንደማንኛውም በሀብቱ ላይ እንዳለ የንብረት መያዣ/የዋስትና ሰነድ ይመዘግባል፣
- ባለሥልጣኑ በዋስትና የተረጋገጠውን ታክስ በሙሉ ሲቀበል ባለሥልጣኑ መዝጋቢው ባለሥልጣን ያካሄደውን ምዝገባ እንዲሰርዘው ማስታወቂያ የሚሰጠው ሲሆን መዝጋቢው ባለሥልጣንም ያለምንም ክፍያ የዋስትናውን ምዝገባ ይሰርዛል።

በሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት ጥያቄ...

- ባንኮች ዋስትና የተቀበሉባቸው ሀብቶች የቀደምትነት መብት የሚኖራቸው ብድሩ ከመሰጠቱ በፊት ታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳ የሌለበት መሆኑ በባለሥልጣኑ የተረጋገጠ ሲሆን ብቻ ነው።

ሙከራ ሶስት

በሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት አብራሩ?



3.10. ሀብትን ስለመያዝ /41/

- ባለሥልጣኑ ታክሱን በመክፈያ ጊዜው ላልከፈለ ማስጠንቀቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ካልከፈለ ሀብት እንዲያዝ ትዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑን የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

- ባለሥልጣኑ ታክሱ የሚከፍል ለመሆኑ ስጋት መኖሩን ካረጋገጠ የመያዣ ትዕዛዙን ለታክስ ከፋዩ ሊሰጥ ወይም የታክስ ከፋዩን ሀብት በይዞታው ሥር ባደረገ ለማንኛውም ሰው ወዲያውኑ ሊሰጥ ይችላል።

ሀብትን ስለመያዝ ....

- የመያዣ ትዕዛዙ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በስተቀር በማንኛውም የታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል፦
  - ✓ በሀብቱ ላይ የቀደምትነት መብት ባላቸው የገንዘብ ጠያቂዎች በተያዘ ንብረት፤
  - ✓ በማናቸውም የፍርድ ሂደት ዕገዳ በተደረገበት ወይም የአፈፃፀም ትዕዛዝ በተሰጠበት ንብረት፤
  - ✓ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ሊታገድ በማይችል ንብረት።

- በታክስ ከፋዩ ንብረት ላይ የመያዣ ትዕዛዝ ከተሰጠ ወይም የሚሰጥ ከሆነ ባለሥልጣኑ በጽሑፍ በሚሰጥ ማስታወቂያ የሚያዘውን ሀብት በሚመለከት በማስረጃነት ሊያገለግል የሚችል ማንኛውንም ሰነድ ወይም መግለጫ የያዘ ማንኛውም ሰው ይህን ሰነድ ወይም መግለጫ ለባለሥልጣኑ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል።

ሀብትን ስለመያዝ...

- በመያዣ ትዕዛዙ መሠረት ንብረት በሚያዝበት ጊዜ የፖሊስ መኮንን በቦታው እንዲገኝ ባለሥልጣኑ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ሲሆን የተያዘውም ንብረት ደህንነቱ በሚረጋገጥበት ሁኔታ እንዲቀመጥ ማድረግ አለበት።

- ባለሥልጣኑ ንብረት በሚይዝበት ጊዜ የተያዘውን ንብረት እና ያልተከፈለውን የታክስ መጠን፤የሚፈለግበትን ታክስ የማይከፍል ከሆነ ሀብቱን በግልጽ ጨረታ እንደሚሸጠው ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ይሰጠዋል።

ሀብትን ስለመያዝ...

- ባለሥልጣኑ ሀብቱን በግልጽ ጨረታ በመሸጥ ከሸያጩ የሚገኘው ገንዘብ በቅደም ተከተል ለሚከተሉት ክፍያዎች እንዲውል ያደርጋል፦
  - ✓ በመጀመሪያ ደረጃ በባለሥልጣኑ በሚወሰነው መጠን ሀብቱን ለመያዝ፣ ለመጠበቅና ለመሸጥ የወጣውን ወጭ ለመሸፈን፤
  - ✓ ማስታወቂያው ላይ የተመለከተውን ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ለመክፈል፤
  - ✓ የታክስ ከፋዩን ሌላ የታክስ ዕዳ ለመክፈል፤
- ከሸያጩ ገንዘብ ላይ ቀሪ ገንዘብ ካለ ንብረቱ ከተሸጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 45 ቀናት ውስጥ ለታክስ ከፋዩ ይከፈለዋል።
- ከሀብት ሽያጭ የሚገኘው ገንዘብ ያነሰ በሚሆንበት ጊዜ ባለሥልጣኑ ቀሪውን ዕዳ ማስከፈል ይችላል።

ሀብትን ስለመያዝ...

- በባለሥልጣኑ የመያዣ ትዕዛዝ የተላለፈበትን ሀብት የያዘ ማንኛውም ሰው ይህንን ሀብት ያላስረከበ/ለማስረከብ ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ ሀብቱን ለመያዝ፣ ለመጠበቅና ለመሸጥ የወጣውን ወጪ ጨምሮ ካላስረከበው ሀብት ዋጋ ሳያልፍ ከታክስ ከፋዩ ለሚፈለገው ታክስ መጠን በግል ተጠያቂ ይሆናል።
- የግብር ከፋዩን ሀብት ለመያዝ የሚቻለው ከሚፈለግበት ግብር ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መጠን ነው።
- የተያዘው/በማሸግ የተከበረው ሀብት የድርጅቱ ደንበኞች ሀብት በውስጡ የሚገኝበት እንደሆነ ሀብቱ ከተያዘ በኋላ ባሉት የተወሰኑ የድርጅቱ የሥራ ቀናትና ሰዓት ደንበኞች ማስረጃቸውን እያቀረቡና ያልተከፈለ አገልግሎት ቀሪ ሂሳብ እየከፈሉ እንዲረከቡ ማድረግ አለበት።

3.11. የተያዘ ወይም የተከበረ ሀብት ስለሚለቀቅበት ሁኔታ

- የተያዘ ወይም የተከበረ ሀብት የሚለቀቀው:-
  - ለሀብቱ መያዝ/መከበር ምክንያት የሆነው የታክስ ዕዳ በሙሉ የተከፈለ እንደሆነ፣
  - ለሀብቱ መያዝ/መከበር ምክንያት የሆነው የታክስ እዳ ዋስትና በማስያዝ በስምምነት የታክስ መክፈያ ጊዜው የተራዘመ እንደሆነ፣
  - የታክስ ዕዳው የተሠረዘ ወይም በምሕረት እንደቀር የተደረገ እንደሆነ፣ ወዲያውኑ ይለቀቃል።

3.12. በተያዘ ወይም በተከበረ ሀብት ላይ የሚቀርብ አቤቱታን ስለመመርመር

- የታክስ ባለዕዳው ወይም ይገባናል የሚሉ ሦስተኛ ወገኖች የተያዘው/የተከበረው ሀብት በሕግ የማይከበር/የማይያዝ ነው በማለት ለባለሥልጣኑ አቤቱታ ሲያቀርብለት አቤቱታው ይጣራል።
- ሀብቱ አላግባብ የተያዘ መሆኑን እና የአቤቱታ አቅራቢው ሀብት መሆኑን በበቂ ማስረጃ ያረጋገጠ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የተያዘው ሀብት እንዲለቀቅ ውሳኔ ይሰጣል።

3.13. የግልጽ ጨረታ አካሄድ ሥነ-ሥርዓት

- የግልጽ ጨረታው ማስታወቂያ ሰፊ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ ይወጣል።
- የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተነገረበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነድ ማቅረብ አለባቸው።
- ሀብቱ የተያዘበት ታክስ ከፋይ ወይም ወኪሉ በተገኘበት ግልጽ ጨረታው ይከፈታል።
- ለግልጽ ጨረታው ከቀረቡት ተወዳዳሪዎች ከፍተኛ ዋጋ የሰጠው የጨረታው አሸናፊ ይሆናል።

3.15. በፋይናንስ ተቋማት የተቀመጠ ገንዘብ እና ንብረት ይዞ ስለማቆየት /42/

- በፋይናንስ ተቋማት የተቀመጠ ገንዘብ እና ንብረት ተይዞ እንዲቆይ የሚደረገው ባለሥልጣኑ በበቂ ምክንያት ከታክስ ከፋዩ ላይ የሚፈለገው ታክስ የሚሰበሰብ ስለመሆኑ ስጋት ሲኖረውና ታክሱ በአስቸኳይ መሰብሰብ ያለበት ሲሆን ይሆናል።
- በፋይናንስ ተቋማት የተቀመጠ ገንዘብ እና ንብረት ተይዞ እንዲቆይ በሚደረግበት ጊዜ ባለሥልጣኑ አንድ የፋይናንስ ተቋም የሚከተሉትን እንዲፈጽም አስተዳደራዊ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፦
- የታክስ ከፋዩ ሂሳቦች እንዳይንቀሳቀሱ እንዲያደርግ፤
- በጥንቃቄ በሚያዙ ዕቃዎች ማስቀመጫ ሣጥን ውስጥ ስለሚገኙ ሀብቶች ተገቢውን መረጃ ወይም በሣጥኑ ውስጥ ያሉትን ሀብቶች ዝርዝር ለባለሥልጣኑ እንዲሰጥ።

ገንዘብ እና ንብረት ይዞ ስለማቆየት...

- በፋይናንስ ተቋሙ ውስጥ ባለ በጥንቃቄ የሚያዙ ዕቃዎች ማስቀመጫ ሣጥን ውስጥ የተቀመጠ ማንኛውም የታክስ ከፋዩ ጥሬ ገንዘብ፣ ውድ ዕቃ፣የከበረ ጌጣጌጥ፣ ወይም ሌላ ንብረት ንብረት እንዳይንቀሳቀስ፤
- ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ፣ ባለሥልጣኑ በታክስ ዓመቱ እና በማናቸውም በቀደመው የታክስ ዓመት ታክስ ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ አስመልክቶ ወዲያውኑ የስጋት የታክስ ስሌት ሊያከናውን ይችላል።
- ባለሥልጣኑ ለፋይናንስ ተቋሙ የዕግድ ትዕዛዝ በደረሰው በ10 ቀናት ጊዜ ውስጥ ትዕዛዙ እንዲቀጥል ለማድረግ የሚያስችል የፍርድ ቤት ፈቃድ ማግኘት አለበት።

3.16. ያልተከፈለን ታክስ ከሦስተኛ ወገኖች ስለማስከፈል

- 3ኛ ወገን ማለት፦ ለታክስ ከፋዩ ባለዕዳ የሆነ፣ በታክስ ከፋዩ ስም ገንዘብ የያዘ፣ለታክስ ከፋዩ የሚከፈል የሌላ ሰው ገንዘብ የያዘ እና ለታክስ ከፋዩ ገንዘብ እንዲከፍል በሌላ ሰው ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው።

- አንድ ታክስ ከፋይ የሚፈለግበትን ታክስ በመክፈያ ጊዜው ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ ገንዘብ ለሚከፍል ሦስተኛ ወገን በጽሑፍ በሚሰጥ ትዕዛዝ የተመለከተውን ገንዘብ ለባለሥልጣኑ እንዲከፍል ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ሲሆን በዚህ ዓይነት የሚከፈለው ገንዘብ ካልተከፈለው የታክስ ዕዳ መብለጥ የለበትም።

ያልተከፈለን ታክስ ከ3ኛ ወገኖች ስለማስከፈል...

- የክፍያ ትዕዛዙ ለታክስ ከፋዩ ገንዘብ የሚከፍል ሦስተኛ ወገን ከደመወዝ ወይም በተወሰነ የጊዜ ገደብ ከሚከፈል ሌላ ተመሳሳይ ክፍያ ላይ ቀንሶ ገቢ እንዲያደርግ በሚሆንበት ጊዜ ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ የሚቀነሰው የገንዘብ መጠን ከሚከፈለው ደመወዝ ወይም ሌላ ክፍያ አንድ-ሶስተኛ መብለጥ የለበትም።
- በጋራ በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ውስጥ የሚገኝን ገንዘብ በተመለከተ የክፍያ ትዕዛዝ ለከፋዩ የሚሰጠው፦
  - የሽርክና ማህበር ሒሳብን ሳይጨምር፣ ታክስ ከፋዩ የሌሎቹ የሒሳብ ባለቤቶች ፊርማ ወይም ፈቃድ ሳያስፈልገው ከሒሳቡ ላይ ገንዘብ ማውጣት የሚችል ሲሆን፤ ወይም

ያልተከፈለን ታክስ ከ3ኛ ወገኖች ስለማስከፈል...

- ሁሉም ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ሲኖርባቸውብቻ ነው።

- የክፍያ ትዕዛዙን መፈፀም ያልቻለ ትዕዛዙ በደረሰው በ7 ቀናት ውስጥ ትዕዛዙን ለመፈፀም ያልቻለበትን ምክንያት በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት። በዚህ መሠረት ባለሥልጣኑ የክፍያ ትዕዛዙን ሊሰርዘው፣ ሊያሻሽለው ወይም ውድቅ ሊያደርገው ይችላል።

- የሚሰጠውን ማስታወቂያ ያለምንም በቂ ምክንያት ያልተቀበለ ሰው በማስታወቂያው ለተመለከተው የገንዘብ መጠን በግሉ ኃላፊ ይሆናል።

- ያልተከፈለን ታክስ ከሦስተኛ ወገኖች ስለማስከፈል በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ሊታገድ በማይችል ንብረት ላይ ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም።

3.17. ከሀገር መውጣትን ለመከልከል የሚሰጥ ትዕዛዝ

- ከሀገር መውጣትን ለመከልከል የሚሰጥ ትዕዛዝ ተፈፃሚ የሚሆነው
  - መክፈል የሚኖርበትን ወይም ወደፊት የሚከፈል ታክስ፤ ወይም
  - ሥራ አስኪያጅ የሆነበት ኩባንያ ወይም ውሳኔ በመስጠት ረገድ የዚህ ሰው ድርሻ ከፍተኛ የሆነበት ኩባንያ መክፈል የሚኖርበትን ወይም ለወደፊቱ የሚከፈል ታክስ፤ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ።
- ከሀገር መውጣትን ለመከልከል የሚሰጥ ትዕዛዝ የሚሰጠው፤
  - ታክስ ለመክፈል የክፍያ ስምምነት ሲያደርግ፤ ወይም

ከሀገር መውጣትን ለመከልከል...

- ማንኛውም ሰው፣ ድርጅት ወይም ኩባንያ ሊከፍል የሚገባውን ወይም ወደፊት የሚከፈለውን ታክስ በሙሉ እስከሚከፍል።
- ፍርድ ቤት ካላራዘመው በስተቀር ከሀገር መውጣትን የሚከለክል ትዕዛዝ ጀምሮ ከ10 ቀናት በኋላ ተፈጻሚ አይሆንም።
- የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ኃላፊ የክልከላ ትዕዛዙ ሲደርሰው ትዕዛዙን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን ይወስዳል።
- ታክስ ከተከፈለ ከሀገር ለመውጣት የሚያስችለው የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

3.18. የንግድ ድርጅትን ለጊዜው ስለማሸግ

- የንግድ ድርጅትን ለጊዜው ማሸግ ተፈፃሚ የሚሆነው አንድ ታክስ ከፋይ በተደጋጋሚ:-
  - በግብር ሕግ መሠረት የሚፈለግበትን ሰነድ ሳይዝ ሲቀር፤ ወይም
  - ታክሱን በመክፈያ ጊዜው ሳይከፍል ሲቀር ይሆናል።
- የንግድ ድርጅትን ለጊዜው ማሸግ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ ታክስ ከፋዩ ማስጠንቀቂያ በደረሰው በ7 ቀናት ውስጥ የሚፈለግበትን ታክስ የማይከፍል ከሆነ ወይም የሚፈለግበትን ሰነድ ያልያዘ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩን የንግድ ድርጅት ለ14 ቀን በጊዜያዊነት የሚያሸግ መሆኑን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

ድርጅትን ለጊዜው ስለማሸግ...

- ባለሥልጣኑ ትዕዛዙን ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ታክስ ከፋዩ የንግድ ድርጅት መግባት የሚችል ሲሆን የማሸጊያ ትዕዛዙ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ የፖሊስ መኮንን በቦታው እንዲገኝ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።
- ባለሥልጣኑ የሒሣብ መዝገብ ሰነዶችን ለመያዝ የሚያስችል በቂ እርምጃ ወስዷል ብሎ ሲያምን እና ታክስ ከፋዩ ታክሱን የሚከፍል ከሆነ የታክስ ከፋዩ የንግድ ድርጅት እንደገና እንዲከፈት ያደርጋል።
- ባለሥልጣኑ በማሸጊያ ትዕዛዝ መሠረት በታሸገው የታክስ ከፋዩ ንግድ ድርጅት ሕንፃ በሚታይ ቦታ ማስታወቂያ ይለጥፋል።

3.19. የተላለፉ የታክስ ዕዳዎች እና በድርጅት ስለሚከፈል ታክስ

- አንድ ታክስ ከፋይ “አስተላላፊ” ተብሎ የሚጠቀስ ከሚያካሂደው የንግድ ሥራ ጋር በተገናኘ ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ያለበት እንደሆነ እና የንግዱን ሀብቶች በሙሉ ወይም በከፊል ግንኙነት ላለው ሰው “ሀብቱ የተላለፈለት ሰው” ተብሎ ለሚጠቀስ ያስተላለፈ እንደሆነ ከንግዱ ሀብት ጋር ተያይዞ ያልተከፈለውን ዕዳ ሀብቱ የተላለፈለት ሰው የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል።

- አንድ ድርጅት ታክሱን በመክፈያው ጊዜ ውስጥ ያልከፈለ እንደሆነ ታክሱ ባልተከፈለበት ጊዜ/ታክሱ ከመከፈሉ በፊት ባሉት 6 ወራት ጊዜ ውስጥ ሥራ አስኪያጅ የነበረ ማንኛውም ሰው ላልተከፈለው ታክስ ከድርጅቱ ጋር የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት ይኖርበታል።

3.20. ማጭበርበር ወይም የታክስ ስወራ ሲፈፀም ስለሚኖር የታክስ ኃላፊነት

- የተመሰከረለት ኦዲተር፣ የተመሰከረለት ፕብሊክ የሒሳብ ባለሙያ ወይም ፕብሊክ ኦዲተር፦
  - ታክስ ከፋዩ ታክስን ለማሳነስ ወይም ታክሱን ለመሰወር እንዲችል የረዳ፣ ያበረታታ፤ የመከረ እንደሆነ፤
  - ታክስ ለማሳነስ ወይም የታክስ ስወራን በሚያስከትል መልኩ በማንኛውም መንገድ እያወቀ ከታክስ ከፋዩ ጋር ከተባበረ ወይም የድርጊቱ አጋር ከሆነ በታክስ ማጭበርበሩ ወይም በታክስ ስወራው ምክንያት ለሚከሰተው የታክስ መቀነስ ከታክስ ከፋዩ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ይኖርበታል።

3.21. ማካካሻ፤ ተመላሽ እና የታክስ ምሕረት

3.21.1. ለታክስ ክፍያዎች የሚሰጥ ማካካሻ

- በታክስ ዓመቱ ከሚፈለግበት የገቢ ግብር ዕዳ በሚበልጥበት ጊዜ ባለሥልጣኑ በብልጫ የታየውን ገንዘብ በሚከተለው ቅደም ተከተል ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፤
- በመጀመሪያ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚቀርን ታክስ ሳይጨምር ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ማንኛውንም ታክስ ለመክፈል ይውላል፤
- ቀሪው ታክስ ከፋዩ በሌላ በማንኛውም የታክስ ሕግ የሚፈለገበትን ታክስ ይውላል፤
- ተራፊ ገንዘብ ካለም ታክስ ከፋዩ በጹሑፍ የተመላሽ ጥያቄ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት ዘጠና (90) ቀናት ውስጥ ለታክስ ከፋዩ ይመለስለታል።

ማካካሻ ...

- ታክስ ከፋዩ በጹሑፍ ስምምነቱን ከገለጸ ገንዘቡ ወደፊት ለሚመጣ ማንኛውም የታክስ ዕዳ መክፈያነት ሊሸጋገር ይችላል።
- ተራፊውን ገንዘብ ለታክስ ከፋዩ ካልከፈለ፣ ዘጠናው ቀን ካለቀ ጀምሮ ተራፊውን ገንዘብ እስከሚመልስበት ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ወለድ የማግኘት መብት አለው።
- የሚከፈለው ወለድ መጣኔ ጊዜው ከመጀመሩ ቀደም ብሎ ባለው ሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ የዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ መጣኔ ይሆናል።

3.21.2. ሊከፈለው ከሚገባው በላይ የተከፈለን ታክስ ስለመመለስ

- ታክስ ከፋዩ ሊከፍል ከሚገባው ታክስ በላይ የከፈለ እንደሆነ በ3 ዓመታት ውስጥ እንዲመለስለት ማመልከት ይችላል።
- ባለሥልጣኑ ሊከፍል ከሚገባው በላይ የከፈለ መሆኑን ሲያምንበት በብልጫ የተከፈለውን የገንዘብ መጠን የሚፈለግበትን ታክስ ለመክፈል እንዲሁም ተመላሽ ይደረጋል። በስህተት ተመላሽ ከተደረገ ለባለሥልጣኑ መልሶ መክፈል አለበት።
- በታክስ ከፋዩ አሳሳችነት ገንዘብ ከተመለሰ በንግድ ባንኮች ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ መጣኔ ላይ 15% ተጨምሮበት ክፍያው ለዘገየበት ጊዜ ወለድ የመክፈል ኃላፊነት አለበት።

2.21.3. ከባድ ችግር ሲያጋጥም ስለሚሰጥ የታክስ ምሕረት

- የታክስ ምሕረት ተፈፃሚ የሚሆነው፤
  - ከባድ የግል ችግር (የተፈጥሮ አደጋ) እና በታክስ ከፋዩ ሞት ምክንያት ታክስ ከፋዩ መክፈል የሚኖርበት ታክስ በሙሉ እንዲከፍል ማድረግ በታክስ ከፋዩ ጥገኞች ላይ ከባድ ችግር የሚፈጥር መሆኑን ሲያምንበት ነው።

ሙከራ አራት

- ታክስን እና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል እና ለዘገየ ክፍያ የሚከፈል ወለድን ግለጹ?
- ማካካሻ፣ ተመላሽ እና ከታክስ ዕዳ ነጻ ስለመሆን ግለጹ?

ማጠቃለያ

- ከግብር ነፃ ከሆኑ ገቢዎች በስተቀር ገቢ ያገኘ በአዋጁ መሠረት ግብሩ በታክስ ስሌት እንደሚከፍል ቀርቧል።
- ታክስ በወቅቱ ስለሚሰበሰብበት ሁኔታ እና ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ለመሰብሰብ፣ ለማስከፈል የታክስ ባለሥልጣኑ ሕጉን በአግባቡ አውቆ የባለድርሻ አካላትን ሚና በማስተባበር የታክስ አስተዳደሩን ውጤታማ ማድረግ እንደሚቻል ተዳሰዋል።
- ማካካሻ፣ተመላሽ እና ከታክስ ዕዳ ነጻ ስለመሆን የሚመለከቱ ጉዳዮችም ለማየት ተሞክሯል።

- የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2009
- ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበውን የራስ ታክስ ስሌት እንዲያሻሽል ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 144/2011
- የግምት ታክስ ስሌት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 138/2010
- የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር 142/2011
- የታክስ ከፋዩን ሀብት ስለመያዝና ስለመሸጥ የወጣ መመሪያ ቁጥር 6/2011
- Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Tax Administration Proclamation No. 983/2016 Technical



አመሰግናለሁ